ኢፕድ

# አዲስ ዘመን


ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 059 ጥቅምት 29 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

# “በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ ስኬቶች እየተመዘገቡ ናቸው”

- ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ



**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ ስኬቶች እየተመዘገቡ መሆኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ አስታውቀዋል፡፡

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ በአዲስ አበባ ለተከታታይ ሶስት ቀናት ሲካሄድ የቆየው “ከረሃብ ነፃ ዓለም” ዓለም አቀፍ ጉባኤ የማጠናቀቂያ መርሃ ግብር ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል ትክክለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች፡፡ የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ ስኬቶችም እየተመዘገቡ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል ትክክለኛ መንገድ ላይ እንደምትገኝም የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ ግብርናን በማሻሻል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡

መንግሥት የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማጠናከርና ለማዘመን ፖሊሲዎች ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን ገልጸው፤ በዚህም ኢትዮጵያ የገጠማትን የምግብ ዋስትና ችግር መፍታት የሚያስችል ጉዞ ላይ መሆኗን ተናግረዋል።

ግብርናውን በምርምር ከመደገፍ በተጨማሪ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ የሰብል አይነቶች እየለሙ እንደሚገኙ አመልክተው፤ በዚህም ምርታማነትን ማሳደግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

“በኢትዮጵያ የምግብ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የወጪ ንግድ ዕድገቱ ምንጮች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ወቅት ኢትዮጵያ ባለፉት ሦስት ወራት ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች የወጪ ንግድ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቷን አስታውቀዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ የተገኘው ውጤት ማስቀጠል ቢቻል እንኳን በዓመት አምስት ቢሊዮን መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት እምቅ አቅም አኳያ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑንም ያመላክታሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው፤ በሚቀጥሉት ዓመታት 50 እና 100 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ መሠራት አለበት ማለታቸውም የሚታወስ ነው፡፡

በዘርፉ የተገኘው ውጤት ከማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ጋር ግንኙነት አለው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ውጪም ባለፉት ሶስት ወራት ስድስት ነጥብ አራት በመቶ ብልጫ ያለው የውጭ ኢንቨስትመንት መሳብ መቻሉን ተናግረዋል፡፡ የሀገሪቱን የፋይናንሻል ሥርዓት መሻሻልና በትይዩ ገበያው መካከል ያለው ክፍተት ሰፊ እንዳይሆን መሠራቱ ለተገኘው ውጤት ምክንያት መሆናቸውንም ነው ያከሉት፡፡

የወጪ ንግድ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል ግብርናን ማረጋገጥ ለዘላቂ የምግብ ዋስትና መሠረት ነው



**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል ግብርናን ማረጋገጥ ለዘላቂ የምግብ ዋስትና መሰረት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስታወቁ።

ከጥቅምት 26 ጀምሮ ለተከታታይ ሦስት ቀናት በአዲስ አበባ የተካሄደው «ከረሃብ ነጻ ዓለም» ዓለም አቀፍ ጉባዔ የማጠቃለያ መርሃ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በሀገራዊ ሪፎርም አማካኝነት ለአየር ጠባይ ለውጥ የማይበገርና ቀጣይነት ያለው የምግብ ምርታማነትን ለማረጋገጥ ውጤታማ ሥራ እያከናወነች ነው ብለዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለፃ፤ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ድርቅና መሰል ችግሮች የማይፈትኑት ኢኮኖሚ በመገንባት ቀጣይነት ያለው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያ በግብርና ማሻሻያ ላይ ትኩረት ሰጥታ በመሥራቷ ድርቅን መቋቋም የሚችል እንደ ስንዴና ማሽላ ያሉ ሰብሎችን በመዝራት ምርታማነት ማሳደግ ችላለች፡፡

በተለይም 40 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ምቹ የግብርና ምህዳር ተፈጥሯል፤ ከዚህ ቀደም የማይታረሱ የነበሩ መሬቶችን በማረስ ምርታማነትን ማሳደግ መቻሉን ጠቅሰዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory

Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



አቶ ሰለሞን ሶካ

## ኢንዱስትሪዎችና የቢዝነስ ተቋማት አሰሪና ሠራተኛን የሚያገናኙ መድረኮች እንዲፈጥሩ ጥሪ ቀረበ

**ነፃነት አለሙ**

አዲስ አበባ፡- ኢንዱስትሪዎችና የቢዝነስ ተቋማት በየዘርፋቸው አሰሪና ሠራተኛን የሚያገናኙ መድረኮችን መፍጠር አለባቸው ሲሉ በሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሰለሞን ሶካ ጥሪ አቀረቡ።

ደረጃ ዶት ኮም እና ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በጋራ በመሆን በማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ድጋፍ ያዘጋጁት ዐውደ ርዕይ ሲከፈት በሚኒስቴሩ የሥራ፣ ሥራ ስምሪትና ገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሰለሞን ሶካ እንደገለጹት፤ አሰሪና ሠራተኛን በቀጥታ የሚያገናኙ መድረኮች መስፋፋት አለባቸው።

ዐውደ ርዕዩ ኢንዱስትሪውን የማነቃቃት፣ የሀገር ጉልበት የሆነውን ወጣት ወደስራ ለማሰማራት እንዲሁም ሀገር ተወዳዳሪና ኢኮኖሚዋ እንዲጠነከር ለማድረግ አይነተኛ ሚና አለው ብለዋል።

ተመሳሳይ ዐውደ ርዕዮች በዓመት አንዴ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በክልሎች፣ በወረዳዎች፣ በዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ለወጣቱ ተደራሽ እንዲሆኑ በየጊዜው በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎችና የቢዝነስ ተቋማት በየዘርፋቸው አሰሪና ሠራተኛን የሚያገናኙ መድረኮችን መፍጠር አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

በስራ ላይ የሚገኙ ፖሊሲዎች በርካታ የስራ ዕድል በሚፈጥር መልኩ ተዘጋጅተዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የሚመለከታቸው ተቋማትም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ላለፉት ሁለት ዓመታት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ፈርጀ ብዙ አገልግሎት የሚሰጥ የስራ ገበያ መረጃ ስርዓት ገንብቶ ስራ ላይ ማዋሉንም አስታውሰዋል።

ቴክኖሎጂው የስራ ገበያ መረጃን በማቀላጠፍና የሰው ኃይል አቅርቦት እና ፍላጎትን በማጣጣም ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ገልጸዋል።

ዕድሜያቸው ለስራ የደረሱ ዜጎች፣ ወደስራ የገቡ ኢንተርፕራይዞች እና ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በተዘጋጀው የስራ ገበያ መረጃ ስርዓት በመመዝገብ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉና ተጠቃሚ እንዲሆኑም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በዚህ የመረጃ ስርዓት ተመዝግበው የነበሩ ከ43 ሺህ በላይ ወጣቶች ወደስራ እንዲገቡ መደረጉን አስታውሰዋል፡፡

በተጨማሪ የስራ ገበያ መረጃ ስርዓቱ ከዚህ በፊት የነበረውን የመረጃ ተአማኒነት ችግር እንደሚቀርፍ ገልፀዋል።

ጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ከማደራጀት አንስቶ፣ በሚፈልጉት ዘርፍ እንዲሰለጥኑ ማድረግ፣ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሆን የፋይናንስ አቅርቦት፣ የቦታ ወይም የሼድ አቅርቦትን እንደሚያመቻችና ለሌሎች ስራ አጥ ወጣቶችም የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# የቱሪዝም ዘርፍ ለኢኮኖሚያዊ ሽግግር የሚገባውን ድርሻ እንዲያበረክት የሚያስችል የፖሊሲ ክለሳ ተደረገ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አቶ ስለሺ ግርማ

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝም ዘርፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ሽግግር የሚገባውን ድርሻ እንዲያበረክት ለማድረግ የፖሊሲ ክለሳ መደረጉን የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ገለጹ፡፡

በኢትዮጵያ ቱሪዝም ፖሊሲ ክለሳ ላይ ያተኮረ ምክክር መድረክ ከክልልና ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ቢሮ ተወካዮች ጋር ትናንት ተካሂዷል፡፡

አቶ ስለሺ መድረኩን በንግግር ሲከፍቱ እንዳሉት፤ የቱሪዝም ዘርፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ሽግግር የሚገባውን ድርሻ እንዲያበረክት ለማድረግ እና ከሀገራዊ ቁልፍ አጀንዳዎችና የልማት እቅዶች ጋር ለማስተሳሰር እንዲቻል የፖሊሲ ክለሳ ተደርጓል፡፡

በ2001 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ የቱሪዝም ፖሊሲ መከለሱን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ቱሪዝም በዓለም ላይ በፍጥነት በማደግ ላይ ያለ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዓለም አጠቃላይ ጥቅል ምርት 10 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ የቅድሚያ ቅድሚያ ከተሰጣቸው አምስት የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ ቱሪዝም እንዲሆን ተደርጓል ብለዋል።

ዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያስገኝና ኢኮኖሚው ላይ ያለው አበርክቶ እንዲያድግ የተለያዩ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በነባሩ ፖሊሲ ያጋጠሙ ጉድለቶችና የፖሊሲ ክፍተቶችን መቅረፍ፣ ዘርፉ ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ሽግግር የሚገባውን ድርሻ እንዲያበረክት ማስቻል፣ ከሀገራዊ ቁልፍ አጀንዳዎችና የልማት እቅዶች ጋር ለማስተሳሰር የፖሊሲ ክለሳ ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

ፖሊሲው ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን ማድረግ፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ ተቋማዊ አደረጃጀትን በማስተካከል፣ የሕግ ማሕቀፎችን ለመቅረፅ እና የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት፣ በቱሪዝም ሴክተር እና በሌሎች የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ዘርፎች ቅንጅት ማሳደግ፣ ዓለም አቀፍ ክስተቶችን እና ውጫዊ ሁነቶችን ባገናዘበ መንገድ ዘርፉን መምራት ለፖሊሲ ክለሳው በተጨማሪ ምክንያትነት ጠቅሰዋል፡፡

ለዚህ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ረቂቅ የፖሊሲ ክለሳ ዝግጅት መከናወኑን አመላክተው፤ በተከታታይ በረቂቅ ፖሊሲው ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ይደረግበታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በዚህ ሂደትም የሚገኙ ግብዓቶችን በማከል ፖሊሲው ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ እንደሚደረግ ሚኒስትር ዴኤታው ጨምረው ጠቅሰዋል፡፡

በምክክር መድረኩ አዲሱ ረቂቅ ፖሊሲ ቀርቦ ውይይት የተካሄደበት ሲሆን፤ ተሳታፊዎችም ቢካተቱ ያሏቸውን ጉዳዮች አንስተዋል፡፡

የቱሪዝም ፖሊሲ ክለሳው በ2026 ዓ.ም ተወዳዳሪ፣ ዘላቂና ፈተናዎችን የሚቋቋም የቱሪዝም ዘርፍ በመፍጠር ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ተመራጭ መዳረሻዎች መካከል አንዷ ሆና ማየት የሚል ራዕይ አንግቦ የተቀረጸ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

# የቡና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽነትን ማስፋት ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የቡና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽነትን ማስፋት ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ገለጸ። የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የቡናን ምርታማነት ለማሳደግ ከዓለም አቀፉ ኖውማን ካፌ ግሩፕ ጋር ተፈራርሟል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የቡናን ምርታማነት ለማሳደግ ከዓለም አቀፉ ኖውማን ካፌ ግሩፕ ጋር ትናንት ሲፈራረም እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ቡና ምርታማነት ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው። የቡና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽነትን ማስፋት ይገባል።

ስምምነቱም ከአርሶ አደሮች እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ ሀገሪቱ ከቡናው ዘርፍ ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንድታገኝ የሚሠራ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አህመድ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ስምምነቱ በሄክታር የሚገኘውን የቡና ምርት መጠን ለማሳደግ እና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአመራረት ሂደትን ለመከተል ይረዳል።

በሀገር ደረጃ የቡና ምርትና ምርታማነት እያደገ መጥቷል። በዚህ ልክ የግሩፑ የቡና እርሻ መሬትን ምርታማነት ማሳደግ ይገባል። ለዚህም ሲባል ኖውማን ካፌ ግሩፕ ጋር ስምምነት ፈጽመናል ያሉት አቶ ጀማል አህመድ፤ ስምምነቱ ቴክኒካል ድጋፍና የገበያ ተደራሽ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ለቡና ምርት ምቹ ሀገር ነች። ይህንን አቅም ከሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ጋር በመተባበር ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ እንሰራለን ያሉት ደግሞ የኖውማን ካፌ ግሩፕ ሥራ አስፈፃሚ ዴቪድ ኖውማን፤ የኢትዮጵያን ቡና ታሪካዊ አመጣጥ በማስተዋወቅ የገበያ ተደራሽነትን ማስፋት እንደሚቻልም ገልጸዋል፡፡

የምንሠራው ሥራ ቡናን በምርት መጠን፣ በጥራት እና በተደራሽነት ደረጃ ማሳደግ ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ኖውማን ካፌ ግሩፕ 60 ድርጅቶችን በስሩ ያቀፈና በ26 ሀገራት በቡና ገበያ የሚታወቅ ድርጅት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ስምምነቱም ከሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ባለፈ የኢትዮጵያ ቡናን ለማስተዋወቅ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

ስምምነቱም ከወረቀት ያለፈና በመተማመን ላይ የተመሰረተ እንዲሁም የጋራ ተጠቃሚነትን ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ዘርፉን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሳደግ እንደሚቻል ጠቁመዋል።

ዜና

# በክልሉ ከ190 ኪሎ ሜትር በላይ የገጠር ልማት ኮሪደር እየተሠራ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል 192 ኪሎ ሜትር የገጠር ልማት ኮሪደር እየተሰራ መሆኑን የክልሉ የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ ገለጸ፡፡

በሲዳማ ክልል የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ የኮሙኒኬሽን ኃላፊ አቶ ደስታ ዳንጮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሲዳማ ክልል 192 ኪሎ ሜትር የገጠር ልማት ኮሪደር ስራ በማህበረሰቡ ተሳትፎ እየተካሄደ ነው፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተጀመረው የኮሪደር ልማት እንቅስቃሴ በሲዳማ ክልል በእቅድ ደረጃ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ስራ እየተገባ መሆኑን አስታውቀው፤ በመጀመሪያ ዙር የገጠር ልማት የኮሪደር ስራም በፈጣን መንገድ መስመሮች በተለይም ሀገር አቋራጭ አስፋልቶች ያሉበት አካባቢና ክልልን ከክልል የሚያገናኙ መስመሮች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከዚህም አንደኛው ከሀዋሳ እስከ ዲላ የሚገኘው የፈጣን መንገድ መስመር ላይ ሲሆን ይህም 80 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እንዲሁም ከአቦስቶ እስከ ኩላ ቦሬ ድረስ የሚገኘው 46 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው መስመር እና ከሀዋሳ አለታወንዶ እስከ በዳዬ በንታ የ66 ኪሎ ሜትር አስፋልት መስመር ላይ ማህበረሰቡን በማሳተፍ እየተሰራ ነው ያለው ብለዋል፡፡

በዚህም በማህበረሰብ ተሳትፎ መንገድ ዳር ያለው የምንጠራ ስራ በስፋት እየተሰራ ሲሆን መንገድ ዳር ላይ ገባ ብለው የገነቡት እንዲያፈርሱ፣ አጥር ያጠሩት እንዲያነሱና የተተከሉ ዛፎች እንዲነሱ፤ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ከፈታ ስራዎችን የማድረግና ቤት የማፍረስ ስራ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በኮሪደር ልማቱ ለአካባቢው ውበትና ጽዳት፣ በአረንጓዴ ልማት ስራ የሀገር በቀል ዛፎችን ጎን ለጎን ለመትከል የሚያስችል፣ ለአካባቢው ነዋሪ ኑሮን የሚያቃልልና የሚያዘምን መሆኑን ገልጸው፤ ይህንን አጠናክሮ ለማስቀጠል በክልሉ የሀዋሳ ከተማን ጨምሮ በአራቱም ዞኖች የንቅናቄ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

የገጠር ኮሪደር ልማት ስራ በተለይም ለአካባቢው ማህበረሰብ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑን አንስተው፤ በዚህም የኢኮኖሚ መነቃቃት፣ ለተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ በተለይም የገጠሩ ጠጠር መንገድ ማህበረሰቡ እርስ በእርስ እንዲገናኝ እና የተሳለጠ እንቅስቃሴ ለመፍጠር የሚያስችል ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እስካሁን ካለው የገጠር ልማት ኮሪደር ስራ በሕዝብ ተሳትፎ እየተሰራ እንጂ በመንግሥት የተያዘ በጀት አለመኖሩን አንስተው፤ በቀጣይ በቀጥታ ከመንግሥት በጀት ተመድቦለት በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ በተለይም በክልሉ በሚሰሩ ረጃጅም እና የጠጠር መንገዶች አካባቢ ለማስጀመር እቅድ ተይዟል ብለዋል፡፡

# ኢትዮጵያ የሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ አባል መሆኗ የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ ያግዛታል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

**አቶ ደሳለኝ ወዬሳ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአባልነት መመረጧ የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ለማስጠበቅ የሚያግዝ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ደሳለኝ ወዬሳ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ ኢትዮጵያ በዚምባዌ ቪክቶሪያ በተካሄደው ሰባተኛው የአፍሪካ ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች ጉባዔ ላይ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆና ተመርጣለች፡፡

አቶ ደሳለኝ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የሕገመንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ አባል መሆኗ የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ ያግዛታል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ሌሎች አባል ሀገራት የዜጎቻቸውን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ በሕገ መንግሥት ትርጉም የደረሱበትን ደረጃ ለማወቅና ለመተግበር ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻችላታልም ነው ያሉት፡፡

በነበረው መድረክ ኢትዮጵያ በሚቀጥለው ዓመት ዓለም አቀፍ ተሞክሯን የምታካፍልበት መድረክ በአዲስ አበባ ይዘጋጃል ያሉት አቶ ደሳለኝ፤ በመድረኩም የ48 አባል ሀገራት የአጣሪ ጉባዔው ፕሬዚዳንቶችና ከአህጉሪቱ ውጪ የታዛቢነት ሚና ያላቸው ከተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚመጡ እንግዶች ይሳተፋሉ፡፡

አቶ ደሳለኝ አክለውም፤ ኢትዮጵያ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆና መመረጧ በአፍሪካና በዓለም ያለው ተደማጭነቷን ለማሳደግ፤ የጥናትና ምርምር ተቋማትም ተሳትፏቸው እንዲጨምር እንዲሁም የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ለማስከበር የሚረዳ መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

ጉባኤው በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያም ለሥራ አስፈጻሚ አባልነት የሚያበቋት መስፈርቶችን በማሟላት እና የድርሻዋን በመወጣት ተገቢውን አስተዋጽኦ እያበረከተች እንደምትገኝ አስረድተዋል፡፡

መድረኩ የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ለማስተዋወቅ እድል የተገኘበት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አጣሪ ጉባዔውም በተለያዩ ሀገራት በሚካሄደው ኮንፈረንስ በመሳተፍ የሕገ መንግሥት አተረጓጎም ሥርዓትን ለማጠናከር የሚረዱ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በሕገ መንግሥታዊ ፍትህ መስክ የኢትዮጵያ አስተዋፅኦ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታይ ያደርጋል ብለዋል፡፡

የአፍሪካ የሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ እ.ኤ.አ ማርች 15/2017 ጀምሮ በሥራ ላይ ያለና 48 የአፍሪካ ሀገራትን ሕገ መንግሥታዊ ተቋማት በአባልነት ያቀፈ ነው፡፡

# በጉባኤው ሀገራት የብዝሀ ህይወት ሀብታቸውን ለመታደግ በቁልፍ ጉዳዮች ላይ ተስማምተዋል

**ዳግማዊት አበበ**



ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

**መስሰ ማሪዮ (ዶ/ር)**

አዲስ አበባ፡- በ16ኛው የተባበሩት መንግሥታት የብዝሃ ህይወት ጉባኤ ሀገራት የብዝሀ ህይወት ሀብታቸውን ለመታደግ በበርካታ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ ደርሰዋል ሲል የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡

በ16ኛው የተመድ የ2024 የብዝሀ ህይወት ጉባኤ "COP 16" አስመልክቶ የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር መለሰ ማሪዮ (ዶ/ር) ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የጉባኤው ሀገራት የብዝሀ ህይወት ሀብታቸውን ለመታደግ በበርካታ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ያደረጉበት ነው ብለዋል፡፡

ከስምምነቶቹ መካከል «ካሊ ፈንድ» የተሰኘ ዓለም አቀፋዊ አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አዲስ ስምምነት ተጠቃሽ መሆኑን ገልጸው፤ ይህ ስምምነትም ከዲጂታል ሴኩዬንስ መረጃ (ዲ.ኤስ.አይ) ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጋራት የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የካሊ ፈንድ ስምምነት ዋነኛው ጥቅም የመድኃኒት፣ የመዋቢያ፣ የባዮ ቴክኖሎጂ፣ የእንስሳት እና የእፅዋት እርባታ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች ጥቅሞቹን ለታዳጊ ሀገራት እና ለአካባቢው ማህበረሰቦች እንዴት ማካፈል እንዳለባቸው የሚመለከት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በጉባኤው ኢትዮጵያ አፍሪካን ወክላ በርካታ ሃሳቦች ላይ ተወያይታለች። በዚህም ኢትዮጵያ መልካም ትብብሮችን ማጠናከር ችላለች ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ ካነሳቻቸው ሃሳቦች ውስጥ በዋናነት ለታዳጊ ሀገራት ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ ፈንድ ሊደረግ ይገባል የሚል ጉዳይ ላይ በትኩረት ውይይት ተደርጓል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በጉባኤው አፍሪካ የሀብት አሰባሰብ ሥርዓት ውስጥ መግባት አለባት የሚል ጉዳይ መነሳቱንም ገልጸዋል።

የአፍሪካ መነሻ ያላቸው ማህበረሰቦች ብዝሃ ህይወትን ባህላቸውና መብታቸው እንዲጠበቅና የቋንቋ እውቅና ሰነድ መጽደቁ እንደ ውጤት የሚታይ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሌሎች ሀገራት የሚኖሩ ትውልደ አፍሪካዊያን (African Descendents) ባህላዊ የአኗኗር ዘይቤዎችን የሚያካትት እንዲሁም በብዝሀ ህይወት ጥበቃ እና ዘላቂነት ባለው አጠቃቀም ላይ የሚጫወቱትን ጉልህ ሚና እውቅና የሚሰጥ ተጨማሪ ውሳኔም መተላለፉን አስረድተዋል፡፡

በጉባኤው የተወሰኑ ጉዳዮች በይደር ለማየት ስምምነት ላይ ቢደረስም፤ የኩሚንግ ሞንትሪያል የብዝሀ ህይወት ማሕቀፍን አተገባበር ለማሳለጥ የሚያስችሉ ውሳኔዎች ተመዝግበዋል ብለዋል።

በ16ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የ2024 የብዝሀ ህይወት ጉባኤ "COP 16" በኮሎምቢያ ካሊ ከተማ መካሄዱ ይታወሳል። ኢትዮጵያም በጉባኤው ስድስት ልኡካን በመላክ መሳተፏ ይታወቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከረሃብ ነፃ የሆነች ዓለምን ለመፍጠር የተባበረ ዓለም አቀፍ ምላሽ ይፈልጋል!

ረሀብ ዓለማችንን ክፉኛ ከሚፈታተኗት ችግሮች መካከል የሚጠቀስ ነው ። ችግሩ በድህና ኋላ ቀር ሀገራት ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም፤ ግጭቶች እና አለመረጋጋቶች በሚታዩባቸው የዓለም አካባቢዎችም በስፋት ይስተዋላል። በችግሩም ለሞት እና ለስደት የሚዳረጉ ሰዎችም ቁጥር በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

ዓለም የሰውን ልጅ መመገብ የሚያስችል በቂ አቅም እንዳላት ይታመናል፤ ይህንን አቅም በኃላፊነት መንፈስ በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠር ባለመቻሉ፤ ቴክኖሎጂ ከፍ ያለ እመርታ ባሳየበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ረሀብ የዓለማችን አጀንዳ እንደሆነ ቀጥሏል።

በአንድ በኩል የሰው ልጅ ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ትኩረት ከመንፈጉ ጋር በተያያዘ እየተፈጠሩ ያሉ የድርቅ አደጋዎች፣ በሌላ በኩል ሰው ሰራሽ በሆኑ ችግሮች ፣ ግጭቶች እና ጦርነቶች የተነሳ መሬት ጦሙን ማደሩ ፣ ሰዎችም ህይወታቸውን ለማቆየት አካባቢያቸውን ለቀው መሰደዳቸው ለረሀብ አደጋዎች መከሰት ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው።

የኢኮኖሚ እድገትን ታሳቢ ያደረገ የሥነ ሕዝብ ምጣኔ አለመኖር ፣ ምርት እና ምርታማነትን መሰረት ያደረጉ የግብርና ፖሊሲዎችን መተግበር የሚያስችል ቁርጠኝነት ማጣት ፣ ለጠባቂነት የሚያጋልጡ ብዙ ድካም እና ልፋት የማይፈልጉ ፖሊሲዎቻቸው ጥገኛ መሆን ለችግሩ ሌለኞቹ ምክንያቶች ናቸው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ተጨባጭ የትብብር መድረኮች አለመፈጠር ፣ በግብርናው ዘርፍ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት የሚጠይቀው ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ለችግሩ ሰለባ ለሆኑ ኋላቀር የዓለማችን ሀገራት "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" መሆኑ ከችግሩ ለዘለቄታው ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት ፈታኝ አድርጎታል።

የምግብ እህል በራሱ አንድ የፖለቲካ ጫና ማሳረፊያ መሳሪያ እየሆነ የመምጣቱም እውነታ ፤በምግብ እህል እጥረት ውስጥ ያሉ ፣ ለረሀብ ተጋላጭነት ያላቸው ሀገራት ከችግሩ ለመውጣት የሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ዓለም አቀፍ ድጋፍ እንዳያገኙ ተጨማሪ ተግዳሮት እንደሆነባቸውም ይታመናል።

እነዚህን ውስብስብ ችግር ፈትቶ ከረሀብ ነፃ የሆነ ዓለም ለመፍጠር፤ ከሁሉም በፊት የተትረፈረፈ ምርት በሚመረትበት ፣ ገና ብዙ ማምረት በሚቻልበት ዓለም አንድም ሰው በየትኛውም ሁኔታ በረሀብ መሞት እንደሌለበት የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ወሳኝ ነው።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመሻገር ፣ የግብርናውን ዘርፍ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ አቅሞችን/ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋት ፣ በተለይም ኋላቀር የሆኑ ሀገራት በቀላሉ ቴክኖሎጂዎችን በቅናሽ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለዚህ የሚሆን ዓለም አቀፍ ትብብር መፍጠር ተገቢ ነው።

ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ትኩረት መስጠት፣ ሰውሰራሽ በሆኑ ችግሮች ፣ ግጭቶች እና ጦርነቶች የተነሳ መሬት ጦሙን እንዳያድር ፣ ሰዎችም አካባቢያቸውን ለቀው እንዳይሰደዱ ግጭቶችን መከላከል የሚያስችል የተሻለ ዓለም አቀፍ የግጭት አፈታት ሥርዓቶችን ማበጀት እና መተግበርን ይጠይቃል።

ሀገራት የግብርናውን ዘርፍ ምርት እና ምርታማነት ለማሳደግ ለሚቀርጿቸው ብሔራዊ ፖሊሲዎች ስኬታማነት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ፣ ለሚገኙ ውጤቶችም እውቅና መስጠት፣ የምግብ እህል አቅርቦትን የፖለቲካ መሳሪያ ከማድረግ መቆጠብ ፣ጉዳዩን ከሰብአዊነት አኳያ ማየት የሚያስችል አዲስ ምልከታ መፍጠር ያስፈልጋል።

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የመንግሥታትን ፣ የሲቪል ማህበራትን ፣ የዓለም አቀፍ ተቋማትን ፣የግሉን ዘርፍ እንዲሁም የግብርና ቴክኖሎጂ አምራች ኩባንያዎችን በአጠቃላይ የመላው ዓለም የጋራ ትብብር ወሳኝ ነው። ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ በተካሄደው "ከረሃብ ነፃ ዓለም" ጉባዔ ላይ ከረሃብ ነፃ የሆነች ዓለም ለመፍጠር የተባበረ ዓለም አቀፍ ምላሽ ይፈልጋል ማለታቸው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አዲስ አበባ ትናንት፣ ዛሬ እና ነገ

ሚሊዮን ሺበሺ

ከኮሪደር ልማት በፊት ስለነበረችው አዲስ አበባ ታሪክ ነጋሪ አያስፈልገንም:: የአባቶችና እናቶች ምስክርነት አያስፈልገንም:: ምክንያቱም፤ ይህ አንድ ዓመት እንኳን ያልሞላ ታሪክ ነው:: ከኮሪደር ልማቱ በፊት የነበረችውን አዲስ አበባ ‹‹ትናንት›› ለማለት ለአቅመ ማገናዘብ መድረስ ብቻ በቂ ነው:: ትንሽ ታሪክ ለማስመሰል ግን ሦስት ዓመት እንኳን ወደኋላ መለስ እንበልና ጥቂት ማሳያዎችን እንውሰድ::

ከፓርላማ መብራት አንስቶ በቤተ መንግሥቱ በኩል ወደ ሽራተን እና ካዛንቺስ ለመሄድ በቀኝ በኩል ያለውን የእግረኛ መንገድ መያዝ ግድ ነው:: ይህ ገና ሦስትና አራት ዓመት ብቻ የሆነው ታሪክ ነው:: በዚህ መንገድ ላይ ለማለፍ የሰርከስ ልምምድ ሳያስፈልግ አይቀርም ነበር:: አስፋልቱን እና የእግረኛ መንገዱን በምትለየዋ ቀጭን ጠርዝ ላይ እየተንጠለጠሉ ማለፍ የግድ ነበር::

በዚች ቀጭን ጠርዝ ላይ የሚሄድ ሰው ጉዳይ ኖሮት በችኮላ የሚሄድ ሳይሆን፤ ‹‹በዚች ጠርዝ ላይ አልፋለሁ አታልፍም›› ውርርድ ተወራርዶ የሚጫወት ነው የሚመስለው:: ምናልባትም ከርቀት ሆኖ የሚያስተውል ሰው ‹‹ትልቁ ሰውዬ ምን ያጃጅለዋል?›› ሊል ይችላል:: ትልቁ ሰውዬ ግን እንደዚያ የሚሄደው ወዶ ሳይሆን ወይም ለጨዋታ ብሎ ሳይሆን የሚረግጠው ስላልነበረው ነው:: ወደ አስፋልቱ መኪና፣ ወደ እግረኛ መንገዱ ደግሞ ኩሬ ስለሆነ ነው::

ይህንንም የሚያደርጉት ወጣትና ጎልማሳ የሆኑ ጤነኛ ሰዎች ናቸው:: በዕድሜ የገፉ ሰዎች የነበራቸው ዕጣ ፋንታ ቀሚሳቸውን ወይም ሱሪያቸውን ከፍ አድርገው ይዘው፤ በውሃ እየተንቦጫረቁ ማለፍ ነው፤ ለዚያውም ለማለፍ ወረፋ ይዘው ማለት ነው:: የነበረው ችግር ውሃና ጭቃ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ እንደዚያም ሆኖ ጠባብ ነበር:: ወረፋ ይዞ ተራ በተራ የሚታለፍ ነበር:: ዛሬስ?

ዛሬ ከፓርላማ መብራት እስከ ካዛንቺስ ድረስ የሚሄድ ሰው የሚያየው ውብ ነገር ዓይን አዋጅ ሆኖበት ሳያስበው ራሱን ሸራተን ጋ ሊያገኘው ይችላል:: ካዛንቺስ ለመሄድ ትምህርት ሚኒስቴር ጋ ታክሲ ጥበቃ ዝናብ ወይም ፀሐይ ይመታው የነበረ ሰው፤ ዛሬ ግን ‹‹እባክህ ና በነፃ ልውሰድህ›› ቢሉት እሺ አይልም! ምክንያቱም በየመንገዱ የሚያየው ነገር ይበልጥበታል::

አሁን ደግሞ እነሆ ተራው የካዛንቺስ ሆኖ፤ ካዛንቺስ እየተሰራች ነው:: ካዛንቺስ ከመናኸሪያ አካባቢ ጀምሮ እስከ ቶታል፤ ከዚያም እስከ ሐናን ዳቦ እና ዑራኤል የነበረው ትርምስ የትናንት ትዝታ ነው:: ከመናኸሪያ ወደ ቶታል የሚወስደው መንገድ (በተለምዶ ሰንደይ ማርኬት የሚባለው) ሰው እና ተሽከርካሪ ወረፋ ይዞ የሚተላለፍበት ነበር:: ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣና የሚሄድ ብቻ ሳይሆን፤ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚሄዱ ሰዎች ራሱ ወረፋ ይዘው የሚተላለፉበት ነበር:: ስለዚህ በዚያ ሁኔታ እስከ መቼ ይቀጥላል?

አሁን ደግሞ ግማሽ ዓመት እንኳን ያልሞላው ታሪክ እናስታውስ:: ከአራት ኪሎ ወደ ፒያሳ ለመሄድ እስከ ራስ መኮንን ድልድይ ድረስ የነበረውን የእግረኛ መንገድ አስቡት:: ልክ ሸራተን አካባቢ እንዳለው የሰርከስ ልምምድ የሚደረግበት የሚመስል ነበር:: ድንጋይ ድንጋይ እየረገጡ፣ እየተንቀጠቀጡ የሚታለፍ ነበር::

ከዚያችውም ጠባብ የእግረኛ መንገድ ላይ ደግሞ ትንንሽ ንግድ ቤቶች ነበሩበት:: አደናቅፎት ዘመም ያለ ሰው ዕቃ ላይ ሊወድቅ ይችላል:: የአስፋልቱ ጥግ ላይ ደግሞ ባለቤቶቻቸው የት እንደሄዱ የማይታወቅ የቆሙ ተሽከርካሪዎች አሉ:: በዚህ የሲያል መንገድ በሆነ ቀጭን መተላለፊያ ላይ ለማለፍ ወረፋ መጠባበቅ የግድ ነበር:: የእግር መርገጫን አትኩሮ በማየት በጥንቃቄ ማለፍ ነው:: በአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን አያለሁ ብሎ ዓይኑን ወደ ጎን የሚል ካለ መውደቁ አይቀሬ ነው:: ዛሬስ?

ዛሬ ከአራት ኪሎ ፒያሳ ለመሄድ ‹‹ምን ጉዳይ አለህ?›› አይባልም:: መንገዱን ለማየት መሄድ በራሱ ጉዳይ ነው:: እዩኝ እዩኝ ይላል:: ያ እየተንጨዋለሉ የሚታለፍ መንገድ፣ እጅን ከኪስ ከቶ ወደፈለጉበት እያዩ የሚጓዙበት ሆኗል:: ለማለፍ ወረፋ የሚጠባበቁበት ሳይሆን አራትና አምስት ሆኖ ጎን ለጎን መሄድ የሚቻልበት ሆኗል:: ለጤና አስፈላጊ ነው የሚባለውን የእግር ጉዞ ለማድረግ የሚያነሳሳ ብቻ ሳይሆን የሚያስገድድ ሆኗል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን በፓርላማ እንደተናገሩት፤ ለአንድ ሚሊዮን ባለመኪና አስፋልት መንገድ ተሰርቶ፣ ለአምስት ሚሊዮን እግረኛ ግን ትኩረት አልተሰጠም ነበር:: በዚያ ላይ መኪና ያለው ሁሉ ለአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ሁሉ ሞተር ሊያስነሳ አይችልም:: ለጤናም ሆነ ለቅልጥፍና በእግር መሄድ ግዴታ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ:: ለሻይ እና ለምሳ ሲወጣ ሁሉ መኪና ሊያስነሳ አይችልም:: ስለዚህ የእግረኛ መንገዶች ማማራቸው ሊመሰገን የሚገባ ነው::

### ለመሆኑ ግን ትናንት ምን ስንል ነበር?

ዛሬ ላይ የኮሪደር ልማቱ በመሰራቱ እያማረረ ያለው ሁሉ ትናንትም ሲያማርር ነበር፤ ምን እያለ? ‹‹የእግረኛ መንገድ የለም›› እያለ! ‹‹አዲስ አበባ ተግማማች›› እያለ:: እንዴት የአፍሪካ መዲና፣ የዓለም የዲፕሎማት መቀመጫ ሆና... እያለ የሚያማርረው ብዙ ነበር:: ከዓመታት በፊት የነበሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ትልቁ ብሶት የከተማዋ መንገዶች መበላሸት፣ የወንዞች ዳርቻ መጥፎ ሽታ፣ በየመንገዱ ያሉ ቤቶች ደረጃቸውን አለመጠበቅ፣ የሽራ እና የዛገ ቆርቆሮ ክምችት ነበር:: እነዚያ ብሶቶች፣ እነዚያ ወቀሳዎች፣ እነዚያ አቤቱታዎች ሰሚ አግኝተው ዛሬ ተቀርፈዋል:: ስለዚህ አዲስ አበባ ዛሬ የምንመኛት ሆናለች ማለት ነው::

### ለመሆኑ አዲስ አበባ ነገ ምን አይነት ትሆናለች?

የዛሬውን የኮሪደር ልማት ያመሰገንነው፣ ያደነቅነው፣ ከትናንት አንፃር ነው:: ስለዚህ የዛሬው ውበት ለነገው ትውልድ አደራ የሚሰጥ ይሆናል ማለት ነው:: የነገውን ትውልድ የሚያነቃ ይሆናል ማለት ነው:: አንድ ጥሩ ነገር ሲጀመር ትልቁ ጥሩነቱ አርዓያ መሆኑ ነው:: ቢያንስ ቢያንስ ከዚህ የተሻለ እንኳን ባይሰራ፣ ከዚህ የባሰ አይደረግም ማለት ነው:: የትናንቱን አይነት አናይም ማለት ነው:: ዛሬ እንዲህ አይነት ከተሰራ ነገ ደግሞ ከዚህ የተሻለ ይሰራል ማለት ነው::

የነገዋ አዲስ አበባ ከዚህም ትበልጣለች ማለት ነው:: ዛሬ ለናሙና ያህል በአራት ኪሎ፣ ፒያሳ፣ ከመገናኛ እስከ ሲ ኤም ሲ፣ ቦሌ፣ መስቀል አደባባይ... በአጠቃላይ በከተማዋ ዋና ዋና መስመሮች ያየናቸው ውብ ሥራዎች ነገ ደግሞ በመላዋ አዲስ አበባ ይሆናል ማለት ነው:: በአንድ ዓመት ውስጥ ይህ ሁሉ ከተሰራ፣ በሚቀጥሉት ዓመታት የምትሰራው አዲስ አበባ ከዚህም በላይ ትሆናለች ማለት ነው:: አራት ኪሎን ወይም ቦሌን አይቶ ወደ ሰፈሩ ሲሄድ ቅር የሚለው ሰው፤ ነገ ሰፈሩም እንደነ ቦሌ ይሆናል ማለት ነው:: ልጆቹ ከተማ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃሉ ማለት ነው::

ከዓመታት በፊት ስለአዲስ አበባ የነበረውን ትርክት ማስታወስ በጣም ቀላል ነው:: በእንግድነት ብቻ የሚያውቋት የክፍለ ሀገር ሰዎች ሳይቀር ‹‹አዲስ አበባ›› ሲባል ወደ አዕምሯቸው የሚመጣ መጥፎ ሽታ ነበር:: ከተማ ሲባል ከመጥፎ ሽታ እና ከመንገድ መጨናነቅ ጋር የሚያያዝ ምስል ፈጥሮ ነበር:: አሁን ግን አዲስ አበባ ለማየት የምታጓጓ፣ ሌሎች ከተሞችንም ለመሥራት የምታነሳሳ ሆናለች ማለት ነው:: ነገ ለመላው ኢትዮጵያ ከተሞች የንጽህና እና የውበት አርዓያ ትሆናለች ማለት ነው:: የነገዋ አዲስ አበባ ከዛሬዋ በላይ አዲስ ትሆናለች!



# ክልሉ የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ ለማፅናት እየሠራ ነው

ፍሬህይወት አወቀ

ሀዋሳ፡- የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ ለማጽናት በርካታ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን የኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ቸሩጌታ ገነነ ገለጹ።

አቶ ቸሩጌታ ይህን ያሉት ትናንት በሀዋሳ ከተማ በተካሄደው ሀገር አቀፍ የሰላም ኮንፈረንስ ላይ ነው። እሳቸው እንዳሉት እንደ ሰላም ሚኒስቴር ሲዳማ ክልል አስተማማኝ ሰላም ያለበት ክልል መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

የሲዳማ ሕዝብ ሰላምን የኖረበትና ጠንቅቆ የሚያውቀው በመሆኑ ሰላሙን ለማፅናትና ለማረጋገጥ በርካታ ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱን ማረጋገጥ ተችሏል ሲሉ አንስተዋል።

ለዚህም በህብረተሰብ ተሳትፎ የተገነቡ የፖሊስ ጽህፈት ቤቶችና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ማሳያ ናቸው በማለት፤ ይህም ለሌሎች ክልሎች ተሞክሮ መሆን የሚችል ስራ ነው ብለዋል።

በህብረተሰብ ተሳትፎ እና በአመራሩ ያላሰለሰ ጥረት የተገነቡት ማዕከላት የህብረተሰቡን ሰላም በማረጋገጥ ረገድ ትልቅ ድርሻ አላቸው ያሉት አቶ ቸሩጌታ፣ ማዕከላቱ በተለይም በቴክኖሎጂ የተደገፉ በመሆናቸው ወንጀልን አስቀድሞ በመከላከል ማህበረሰቡ ዘላቂ ሰላም እንዲኖረው የሚያስችሉ ናቸው ብለዋል።

በሰላም ኮንፈረንሱ የተገኙት የሲዳማ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ደስታ ሌዳሞ እንዳሉት፤ ባለፉት አራት ዓመታት የክልሉን ሰላም ለማስጠበቅ ሰፊ ስራ ተሰርቷል።

ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ የፀጥታ መዋቅርን ማጠናከርና የፀጥታ ተቋማትን መገንባትና በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

የማህበረሰቡ ተሳትፎ ትልቅ ድርሻ ያለው መሆኑን አስታውሰው፤ በቀጣይም ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ሁሉም ሰው ለሀገር ሰላም ዘብ እንዲሆን ጥሪ አስተላልፈዋል።

## የአየር ንብረት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የዘላቂ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ስትራቴጂክ አጋርነትን ይፈልጋል ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ብሔራዊ ፕሮግራም ቀርጻ እየሠራች እንደምትገኝ ጠቅሰው፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ስንዴን ከውጭ ከማስገባት ተላቃ ወደ ውጭ መላክ መጀመሯን ገልጸዋል፡፡

ከጉባዔ ተግባራዊ ምላሽ የሚሹ ግብዓቶች የተገኙበት መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አማካኝነት የተቀናጀ የግብርና ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ውጤታማ ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል። በዚህም ምርታማነትን ማሳደግ ተችሏል ብለዋል፡፡

በተለይም ለሴት አርሶ አደሮች የሚደረገው ድጋፍ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን በመግለጽ፤ ረሃብ የተባበረ ዓለም አቀፍ ምላሽን ይፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ የተቀናጀ ምላሽ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ የተለመደውን የግብርና ዘዴ መቀየርን ጨምሮ ድርቅን መቋቋም የሚችሉና ምርታማ የሆኑ ዘሮችን በመዝራት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ረሃብን ማስወገድ የጋራ ጥረትን የሚፈልግ ጉዳይ መሆኑን አፅንዖት ሰጥተዋል፡፡

ከረሃብ ነጻ ዓለም ለመፍጠር የሚከናወኑ ሥራዎችን የሚደግፍ ዓለም አቀፍ ፈንድ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ በፖሊሲና በስልጠና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ግብርናን ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ የምግብ ዋስትናን በቀጣይነት ለማከናወን በቴክኖሎጂ፣ በስልጠና፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ግብርና አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

አነስተኛ አርሶ አደሮች ለዓለም የምግብ አቅርቦት የጀርባ አጥንት ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴን ወደ ዘመናዊ እንዲቀይሩ ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ አነስተኛ አርሶ አደሮችን ለመደገፍ የገንዘብ ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡ እንዲሁም አካታች የፋይናንስና የገበያ ሥርዓትን መዘርጋት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

## "በኢትዮጵያ የምግብ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ራሷን በምግብ ለመቻል የሚያስችላት ጉዞ ላይ ናት ያሉት ፕሬዚዳንት ታዬ፤ የዓለም ችግር የሆነውን ረሃብ ለማስወገድ ከጋራ ጥረት ጎን ለጎን ምርታማነትን ለማሳደግ ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነትና አጥጋቢ የፋይናንስ ድጋፍ መኖር እንዳለበት አንስተዋል፡፡

ከርሃብ ነፃ የሆነ ዓለምን ለመፍጠር የፖለቲካዊ ቁርጠኝነት አስፈላጊ መሆኑን አውስተው፤ ይህም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለሚከናወኑ ሥራዎች ሕዝብን ለማስተባበርና ለማሳተፍ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ጠቅሰዋል።

ረሃብ አልባ ዓለምን ተግባራዊ ለማድረግ የአፍሪካ ሀገራት በቂ በጀት መመደብና ራሳቸውን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ ማብቃት እንዳለባቸው አብራርተዋል፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፤ ረሃብን ከዓለም ለማስወገድ በአፋጣኝ ወደ ተግባር መግባት ተገቢ ነው፡፡ የምግብ ዋስትናንና የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማረጋገጥ ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን በቴክኖሎጂና በፋይናንስ መደገፍ ከረሃብ ነጻ ዓለምን ለመፍጠር አጋዥ ነው፡፡

አፍሪካ እምቅ አቅሟን አሟጣ በመጠቀም አስከፊውን ረሃብ ለማስወገድ በአንድነት መነሳት አለባት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ረሃብን መዋጋት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ከረሃብ ነፃ ዓለም ለመፍጠርና ተግባራዊ እርምጃዎችን ወደ ውጤት ለመቀየር ባለራዕይ መሪዎችን ማብዛትና ትርክትን መቀየር ወሳኝ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ጉባኤው የዘላቂ ልማት ግቦችንና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንቅፋት የሆኑ ችግሮች የተለዩበት መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

## የወጪ ንግድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ለገሰ እንደሚሉት፤ በቅርቡ የተሻሻለው የማክሮ ኢኮኖሚ የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በተለይ የውጭ ምንዛሪው በገበያው እንዲወሰን መደረጉ ለተገኘው ውጤት የጎላ ድርሻ አለው፡፡

ማሻሻያው መደረጉ ላኪዎች የኢትዮጵያን ምርቶች ወደ ተለያየ ሀገራት ገበያ ሲልኩ ከሌላው በላይ የመወዳደር እድል ስለሚሰጣቸው የሀገሪቱ የወጪ ንግድ ለማደግ ምክንያት ነው የሚሉት ባለሙያው፤ በዚህ የተነሳም ያደጉ ሀገራት ዋጋቸው እምብዛም እንዳይጨምር እንደሚያደርጉ ይጠቁማሉ፡፡ ለአብነትም ጃፓን፣ ቻይና ደቡብ ኮሪያ አንድ የአሜሪካ ዶላር ከ120 እስከ አንድ ሺህ 300 ድረስ ይመነዘራል፡፡

በሩብ ዓመቱ የወጪ ንግድ 132 በመቶ ወይም ከ700 ሚሊዮን ዶላር በላይ ጨምሯል ያሉ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት በዓመት ኤክስፖርት ተልኮ የሚገኘው ገቢ ነዳጅ ገቢ ለማድረግ እንኳን የሚሸፍን አለመሆኑን ያክላሉ፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሪፎርሙ ከመካሄዱ በፊት ወርቅ የሚሸጥለት አጥቶ ከዓለም ገበያ እስከ 72 በመቶ ጨምሮ ይገዛ ነበር፡፡ በተጨማሪም የቀንድ ከብቶች በጎረቤት ሀገራት በኩል በሕገወጥ መንገድ ኤክስፖርት ይደረጉ የነበረውን ወደ ትክክለኛው ማሕቀፍ እንዲመጡ አድርጓቸዋል፡፡

በብሔራዊ ባንክ የተሻሻለው የባንኮች ዶላር መግዣና መሸጫ መካከል ያለው ልዩነት ከሁለት በመቶ እንዳይበልጥ መወሰኑ ለኢኮኖሚው ማሻሻያ ተጨማሪ እድል ይዞ የሚመጣ ነው የሚሉት ባለሙያው፤ ብሔራዊ ባንክ የመሪነት ሚናውን በማጠናከር ከዚህ የበለጠ ማሻሻያዎችን ማድረግ እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ፤ ማሻሻያው እንደተደረገ ባንኮች በአንድ ዶላር ያተርፉ የነበሩት አንድ ብር ከ90 ሳንቲም አካባቢ ቢሆንም በ15 ቀናት ልዩነት ውስጥ 12 ብር ደረጃ አድጎ እንደነበር ጠቅሰው፤ ይህም አስመጪው ያመጣው ዕቃ ላይ ጨምሮ ስለሚሸጥ ጉዳቱ ለህብረተሰቡ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ አስመጪና ላኪዎችን ሊጎዳ የሚችል ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ብሔራዊ ባንክ ህብረተሰቡ ከመጎዳቱ በፊት ቀድሞ ኢኮኖሚውን እያነበበ መሰል ውሳኔዎችን መውሰድ እንዲሁም አስመጪዎች ዶላር ለመግዛት ሲፈልጉ ለባንኮች የሚከፍሏቸው የኮሚሽን ክፍያዎች ግልጽ ሆነው መነሻና መድረሻ ሊቀመጥላቸው እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

አሁን ላይ በዘርፉ የተገኘው ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው ብሔራዊ ባንክ በተለይ የንግድ ባንኮች የብድር አቅርቦት እና የዶላር ፍሰት ላይ እየሰሩ ያሏቸው ስራዎች ምንድነው፤ አካታችነታቸውስ ምን ያህል ነው የሚሉት ላይ ማጣራት አስፈላጊ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

እንደ ሀገር ለብድር ከቀረበው ብር ውስጥ ከ23 በመቶ በላይ የሚሆነው 10 የሚሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ብቻ መውሰዳቸውን ብሔራዊ ባንክ ያወጣው ሪፖርት እንደሚያመለክት ያስረዳሉ፡፡

ማሻሻያው በተለይ ዜጎች መቋቋም የማይችሉት የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበት እንዲሁም አስመጪዎችን በከፍተኛ ደረጃ የጎዳ ስለመሆኑ ይናገራሉ፡፡

በሩብ ዓመቱ ከወጪ ንግድ የተገኘው እምርታዊ ለውጥ ከባለፉት 50 ዓመታት ጀምሮ ሲደረጉ የነበሩ ማሻሻያዎች እንጂ በኢኮኖሚው ማሻሻያ የመጣ ነው የሚል ግምት እንደሌላቸው የገለጹት ደግሞ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና የፖሊሲ አማካሪ ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

የዚህኛው ማሻሻያ ግን ውጤቱን ለማግኘት የተወሰኑ ጊዜያት የሚፈልግ ነው የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ይሁን እንጂ ማሻሻያው ካፒታል ገበያውን ለማሳደግና የውጭ ኩባንያዎች ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ እየፈጠረ ነው ይላሉ፡፡

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ ከማሻሻያው ጎን ለጎን ሰላምና ጸጥታው የሚረጋገጥ ከሆነ የሀገሪቱ የወጪ ንግድ ከፍተኛ ተስፋ የሚጣልበት ነው፡፡ ከዚህ በፊት ከሚላኩ ምርቶች በተጨማሪ ሌሎች ለኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶችን በስፋት አምርቶ መላክ ያስፈልጋል፡፡

ብዙ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች ከቢሮክራሲ ጋር በተያያዘ ምሬት ሲያሰሙ ይስተዋላሉ ያሉ ሲሆን፤ የተገኘውን ውጤት ለማስቀጠልም ቢሮክራሲ ማስወገድ፣ ቀልጣፋ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም ሰፋፊ የምርመራ ዘገባዎች መሠራት እንዳለበት ይናገራሉ፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ብሪክስ እና ወጣቶች

ክብረአብ በላቸው




የአባል ሀገራቱን የመጀመሪያውን ፊደል ይዞ የተመሠረተው ብሪክስ ምህጻረ ቃል ነው፡፡ ምህጻረ ቃሉ መጠሪያ ሆኖ ያገለገለው፤ ብራዚልን፣ ሩሲያን፣ ሕንድን፣ ቻይና እና ደቡብ አፍሪካን አካቶ ነው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ይህን ስያሜ የሰጡት እ.ኤ.አ በ2001 የጎልድማን ሳክስ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ጂም ኦ'ኔል እንደሆኑ ይነገራል።

በወቅቱ የብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድ እና ቻይና ኢኮኖሚ ከፍተኛ እምርታ ማሳየቱን ተከትሎ፤ የዓለምን ኢኮኖሚ የሚለውጥ አቅም እንዳለው በመገንዘባቸው በጉዳዩ ላይ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶበት ነበር።

ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የባለብዙ መድረኩ ብሪክስ አባል ሀገራት የዓለምን ሕዝብ 45 በመቶ እና የዓለምን የሀገር ውስጥ ጥቅል ምርት 31 ከመቶ ይሸፍናሉ። የብሪክስ ዋናው ግብ ቀጣይነት ያለው፣ ፍትሃዊ እና ለሁሉም የሚጠቅም እድገትን ለማስፈን በአባል ሀገራቱ መካከል ያለውን ትብብር ማሳደግ፣ ማጠናከር እና ማስፋት እንደሆነም ይነገራል።

የአባላቱ ድምር ምጣኔ ሀብት ከ28 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ አለው። ከዓለም ኢኮኖሚ 28 በመቶውን ማለት ነው። ኢራን፣ ሳዑዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስን በአባልነት የሚያካትተው የብሪክስ አገራት ቡድን 44 በመቶ የሚሆነውን ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት ያመረትበታል። ቡድኑ የምዕራባውያን አገሮች እንደ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም እና የዓለም ባንክ ያሉ እንዲሁም ለመንግሥታት ብድር የሚሰጡ ጠቃሚ ዓለም አቀፍ ተቋማትን እንደሚቆጣጠሩ ይከራከራሉ።

ከዚህ አንጻር በመልማት ላይ ያሉ አገራት "የበለጠ ድምጽ እና ውክልና" እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። እ.አ.አ በ2014 የብሪክስ አገራት መሠረተ ልማትን ለማሳደግ የሚያግዝ ገንዘብ የሚያቀርብ አዲስ ልማት ባንክ አቋቁመዋል። እ.አ.አ በ2022 መገባደጃ ላይ ለአዳዲስ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የባቡር መስመሮች እና የውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች 32 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ለአገራት አቅርቧል።

ሦስት ቢሊዮን የሚጠጋ የዓለም ሕዝብ የሚኖረው በጥምረቱ ሀገራት ውስጥ ነው። በአንፃሩ የቡድን ሰባት አባል ሀገራት ተብለው የሚታወቁት ምዕራባውያን ሀገራት ከዓለም ጠቅላላ ምርት ድርሻቸው 30 ነጥብ አምሥት በመቶ ነው። ይህ የሚያሳየው የብሪክስ ሀገራትን ከፍተኛ አቅም ነው።

ኢትዮጵያም ይፋዊ ጥያቄ አቅርባ ይህን ጥምረት ባለፈው ዓመት መቀላቀሏ ይታወሳል። የኢትዮጵያ የአባልነት ጥያቄዋ ተቀባይነት ያገኘው ከሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄ ካቀረቡ 20 ከሚበልጡ ሀገራት ጋር ጠንካራ ፉክክር አድርጋ የተሻለች ሆነ በመገኘቷ ነው። ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ ተቋማት በአባልነት እና መስራችነት የረጅም ጊዜ ታሪክ እና ልምድ ያለት ሀገር መሆኗ በ‹‹ብሪክስ››ም ዘንድ ተፈላጊ አድርጎታል።

ብሪክስ የተቋቋመበት አንዱ ዓላማም ኢኮኖሚዊ ዕድገትን የተመለከተ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ፣ ከአፍሪካ በሕዝብ ብዛት ሁለተኛ መሆኗ እና ተከታታይ እድገት እያስመዘገበች ያለች መሆኗ የ‹‹ብሪክስ›› አባል ሀገራት ከተሰባሰቡበት ዓላማ ጋር የተሰናሰለ መሆኑ ወደ ብሪክስ ላደረገችው ጉዞ አቅም እንደሆነት ይታመናል።

ይህ የብሪክስ ጥምረት በቅርቡ በሩሲያ ካዛን ከተማ የጥምረቱ የወጣቶች ምክር ቤት ስብሰባ አድርጓል። ኢትዮጵያም በስብሰባው ተሳትፎ አድርጋለች። በስብሰባው ከኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት እና ከሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተውጣጣ የልዑክ ቡድን ኢትዮጵያን ወክሎ ተሳትፏል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤትን በመወከል የምክር ቤቱ የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ወጣት ይሁነኝ መሀመድ በስብሰባው ተሳተፈ ነበር። ወጣት ይሁነኝ ከጉባኤው መልስ ከአዲስ ዘመን ጋር በነበረው ቆይታ ጉባኤው በብዙ መልኩ የተሳካ እንደነበርና የኢትዮጵያ ወጣቶችን ፍላጐትና አቅም ለማስረዳት ዕድል የተገኘበት ስለመሆኑ ተናግሯል።

በጉባኤው የጥምረቱ መሪዎች የደረሱባቸውን ስምምነቶችና መግለጫዎች መሠረት በማድረግ እነርሱ ላይ ውይይት በማድረግ ነው ጉባኤው ጅማሮውን ያደረገው የሚለው ይሁነኝ፤ በአባል ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች አንድነታቸውን ለማጠናከር ምን አይነት ሥራዎች መሥራት ይጠበቅባቸዋል በሚሉ ጉዳዮች ሰፊ ውይይት በማድረግ የወጣቶች ጉባኤው የመጀመሪያ ቀን ውሎ እንዳሳለፈ ይናገራል።

የእያንዳንዱ አባል ሀገር ተወካይ ወጣቶች ሀገራቸው በጥምረቱ አማካኝነት ማግኘት ስላለባቸው ጥቅም የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት ውይይት ስለማድረጋቸው የሚናገረው ይሁነኝ፤ ኢትዮጵያም በዚህ ሕብረት መቀላቀሏ እንዳለ ሆኖ ማግኘት ስለምትፈልገው ጥቅም በማንሳት የኢትዮጵያ ፍላጐት እንዲሰማ ጥረት እንደተደረገ ይናገራል።

በተጨማሪም የሀገራቱ የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲያድግ የሚያግዙ ውይይቶች ስለመካሄዳቸው የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ፤ የጥምረቱ አንዱ ዓላማ በአባል ሀገራቱ ሕዝቦች መካከል የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መፍጠር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ወጣቶች ስለሚኖራቸው ሚና በማንሳት የተደረጉ ውይይቶች ሀገራቱ ከኢኮኖሚያዊ ትብብር ባለፈ ጠንካራ ወዳጅነት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ናቸው ይላል።

የጥምረቱ ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ፤ ጥምረቱ ጉዞው የተሳካ እንዲሆን የወጣቶች ሚና ጉልህ ነው፡፡ ነገ የብሪክስ መሪዎች እና በጥምረቱ ውስጥ የሚቋቋሙ ተቋማትን የሚመሩት ወጣቶች ናቸው፤ ይህንን ኃላፊነት መውሰድ ከወጣቶች ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አኳያ ጉባኤው የጥምረቱ አባል ሀገር ወጣቶች እራሳቸውን ብቁ እንዲያደርጉ መልዕክት የተላለፈበት እንደሆነ ይገልጻል።

የአባል ሀገራቱ ወጣቶች እየተጋፈጡ ያሉባቸው ችግሮች ተለይተው የመፍትሔ ሀሳብ ለማምጣት ውይይት እንደተደረገ የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ፤ በተለይም ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ በተለይ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ ለማመቻቸት ከፍተኛ ጥረት እንደተደረገ ይናገራል።

ወጣት ይሁነኝ፤ በትምህርትና ስልጠና፣ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንዲሁም በጤናና ሰው ሰራሽ አስተውሎት መስክ ያሉብንን ውስንነቶች ለመሙላት በዘርፉ የላቀ የስልጣኔ ደረጃ ላይ ከደረሱ እንደ ቻይና፣ ሩሲያና ሕንድ ተወካዮች ጋር ፍሬያማ ውይይቶች አድርገናል ይላል፡፡ እነዚህ ውይይቶች እየዳበሩ ሄደው የኢትዮጵያን ወጣቶች ተጠቃሚነት እንደሚያሳድጉ ይናገራል።

‹‹አሁን በይፋ የማልገልፃቸው ግን በጥምረቱ አባል ሀገራት ተግባራዊ የሚደረጉ ከ10 በላይ ፕሮጀክቶች አሉ›› የሚለው ወጣት ይሁነኝ፤ ``እኛም ሀገርን ወክሎ በጉባኤው ተሳታፊ እንደሆነ ወጣት ከተሳትፎ ባሻገር እነዚህ በእቅድ ደረጃ ያሉ ፕሮጀክቶች በኢትዮጵያ እንዲተገበሩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አድርገናል፤ በተጨማሪ በዚህ ስብሰባ ምን ማሳካት አለብን የሚለውን እቅድ አውጥተን ነው ወደ ሩሲያ ካዛን የተጓዝነው፤ ከዚህ አኳያ ቆይታችንም የተሳካ ነበር ይላል።

ወደ እዚህ ጥምረት ለመቀላቀል እንደ መንግሥት የተወሰደው ውሳኔ የሚደነቅ ስለመሆኑ የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ወደፊት እንደርስበታለን ብለው ላቀዱት ብልፅግናና እድገት እንደ ብሪክስ ወዳሉ ሀገራት ጥምረት ተቀላቅሎ የንግድ አማራጮችን ማስፋት ለነገ የማይባል ሥራ መሆኑን ይናገራል።

ብሪክስ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በዓለም ላይ ትልቁ ጥምረት ይሆናል፡፡ ብዙ ሀገራት ወደ ጥምረቱ ለመቀላቀል ጥያቄ እያቀረቡ ነው። ከ120ሚልዮን በላይ ሕዝብ ያላት ኢትዮጵያ ከድህነትና ኋላቀርነት ተላቃ ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት ከፈለገች ባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ማጠናከርና ወዳጅ ማብዛት የውዴታ ግዴታዋ ነው ይላል።

እንደቻይናና ሩሲያ ያሉ ሀገራት በቴክኖሎጂ ልማት ከፍተኛ የሚባል የእድገት ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገራት ስለመሆናቸው የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ፤ በአንፃሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በዘርፉ እድገት ወደኋላ የቀሩ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ዛሬ የላቀ ብልፅግና ላይ የደረሱ ሀገራት ምን አይነት መንገድ ተከትለው በመጓዝ ውጤታማ መሆን ቻሉ የሚለው ተነስቶ ልምድ የሚቀሰምበት መድረክ በመሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ ነው ይላል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት፣ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ መሆኗ፣ በአፍሪካ ቀንድ የቀይ ባሕር ጂኦ ፖለቲካዊ አቀማመጥና በቀጣናው ተፅዕኖ ፈጣሪ ናት። ይህ በዚህ ሕብረት ለመቀላቀሏ ምክንያት ነው የሚለው ወጣት ይሁነኝ፤ ይህንን መልካም አጋጣሚ ደግሞ ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም ማዋል እንደሚያስፈልግ ይናገራል።

ወጣት ይሁነኝ እንደሚናገረው፤ ጥምረቱ የአንድ ወገን የበላይነትን በመገዳደር ሚናው ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ እያደገች ያለች ሀገር እንደመሆኗ ወደዚህ ጥምረት መግባቷ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን የመደራደር አቅም ከፍ ያደርግላታል። ከፖለቲካ እና ኢኮኖሚ አንፃር ፋይዳው የጎላ ነው፤ በተጨማሪም ሀገሪቱ ወደውጭ ለምትልካቸው ምርቶች ተጨማሪ የገበያ አማራጭ ያስፈልጋታል። በእነዚህ እና ሌሎች መሰል ምክንያቶች የጥምረቱ አባል መሆን ጠቀሜታው እንደ ሀገር ከፍተኛ ነው።

ጥምረቱ የራሱ የመገበያያ ገንዘብ ይፋ በማድረግ ከዶላር ጥገኝነት ነፃ የሆነ የዓለም የኢኮኖሚ ስርዓት ለመፍጠር ጥረት እያደረገ እንዳለ የሚናገረው ይሁነኝ፤ በተጨማሪም በጥምረቱ ውስጥ የተካተቱ ሀገራት እርስበርስ በሚኖራቸው የንግድና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በየራሳቸው ሀገር ገንዘብ መገበያየት እንዲችሉ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ ይህ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለሚገዳደራቸው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ትልቅ ተስፋ ነው ይላል።

እንደኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት በተለይ ከሥራ ዕድል ፈጠራና ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ ከቻይናና ሩሲያ ተወካዮች ጋር ሰፊ ውይይቶችን ስለማድረጋቸው የሚናገረው ወጣት ይሁነኝ፤ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ መዋለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ በሀገሪቱ ስላሉ የኢንቨስትመንት አማራጮች ሰፊ ገለፃ በማድረግ ሂደት የካዛን የብሪክስ ወጣቶች ምክር ቤት ጉባኤ ውጤታማ እንደነበር ይናገራል።

ለኢትዮጵያ ወጣቶች የተለያዩ የስልጠና ዕድሎች እንዲፈጠሩ ጥረት ተደርጓል የሚለው ወጣት ይሁነኝ፤ አቅም ያላቸውን ወጣቶች ኢትዮጵያ በምትፈልገው መስክ የትምህርትና ስልጠና ዕድል እንዲያገኙ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ይህ የክህሎት ክፍተትን በመሙላት ኢትዮጵያ ለመለወጥ በምታደርገው ጉዞ አጋዥ እንደሚሆን ተነግሯል።

ወጣት ይሁነኝ እንደሚናገረው፤ የዓለም ፖለቲካ እና አሰላለፉ እየተቀያየረ እየሄደ ነው። በተፈጥሮውም ተቀያያሪ ነው። በአንድ ቦታ የሚቆም አይደለም፤ ተለዋዋጭ ነው። በዚህ ተለዋዋጭ የዓለም ፖለቲካ ኢትዮጵያ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ የምትችልበትን አማራጭ ሁሉ መጠቀም አለባት፤ ከአንድ ወገን ጋር ብቻ ሕብረት በማድረግ የሚፈለጉ ብሔራዊ ጥቅሞች ማሳካት የሚቻል አይደለም ይላል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት እንደ ተቋም የኢትዮጵያ ወጣቶች በጥምረቱ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም ዕድሎች መጠቀም እንዲችሉ ጥረት ያደርጋል የሚለው ይሁነኝ፤ ከዚህ አኳያ ወጣቶች በተለይ ቴክኖሎጂን መረዳት የሚችሉ ሆነው እራሳቸውን ማብቃት እንዳለባቸው መልዕክቱን አስተላልፏል።

# የምድር በረከት

## አበረታች ለውጦች እየታየበት ያለው የወርቅ ግብይት

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የማዕድን ሀብት ክምችት ያላት ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ ማዕድናት መካከል አንዱ ወርቅ ሲሆን አገሪቱ ከፍተኛ መጠን ያለው የወርቅ ክምችት እንዳላት በጥናት ተረጋግጧል፡፡ እስካሁን በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ክምችት መገኘቱን ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ ወርቅ ሲባል ሁለት አይነት ነው፡፡ ጽንሰ ወርቅ እና ደለል ወርቅ ተብሎም ይጠራል፡፡ ደለል ወርቅ ከላይ ያለው ድንጋይ በተለያዩ ምክንያቶች ሲበሰብስና ሲፈረካከስ ከዚያ ውስጥ ሊወጣ የሚችል የወርቅ አይነት ነው፡፡ ይህንን አይነቱ ወርቅ አብዛኛውን ጊዜ ከተራራ ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ በውሃ ወይም በንፋስ ዝቅ ወዳለ ቦታ እየሄደ ላይ መጥቶ ይከማቻል፡፡ ይህም በአነስተኛ ቴክኖሎጂና በትንሽ ወጪ ሊመረት ይችላል፡፡ የደለል ወርቅ ጊዜያዊ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ሊያልቅ ይችላል፡፡

ጽንሰ ወርቅ መሬት ውስጥ በጣም ወደታች ተገብቶ የሚወጣና ተፈጭቶ በትልቅ ቴክኖሎጂ የሚመረት ነው። ትልቅ የሚባለውም ጽንሰ ወርቅ ነው፡፡ አሁን ላይ ያለው መረጃ እንደሚያሳየው የደለል ወርቅ በዚህ ደረጃ አለ ማለት ትልቅ ክምችት ያለው ጽንሰ ወርቅ እንዳለ አመላካች ነው፡፡ ጽንሰ ወርቅ በጥልቀት በትልቅ ቴክኖሎጂ እና ረጅም ጊዜ (ከ30 እስከ 50 ዓመታት) የሚፈልግ ነውና ያለው ክምችት ቀላል የሚባል እንዳልሆነ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡



ጽንሰ ወርቅ ከፍተኛ ሀብትና ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ እንደመሆኑ ከፍተኛ አቅም ባላቸው ትላልቅ ኩባንያዎች የሚሰራ ነው፡፡ የወርቅ ማዕድን ሀብት በትግራይ፣ በቤኒሻንጉል ክልል፣ በጋምቤላ፣ በኦሮሚያና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና በሌሎችም ክልሎች በስፋት ይገኛል፡፡ በሀገራችን ጥቂት ኩባንያዎች ናቸው በዚህ ልማት የተሰማሩት፡፡ በአብዛኛው በደለል ወርቅ ልማት ላይ በባህላዊ መንገድ የማልማት ስራ ነው እየተከናወነ ያለው፡፡

መንግሥት የማዕድን ዘርፍ ለአገር ኢኮኖሚ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦና ለዜጎች ከሚፈጥረው የሥራ እድል አንጻር በመመልከት በሰጠው ትኩረት ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ እንዲሆን መደረጉ ይታወቃል፡፡ ይህን ተከትሎም የማዕድን ሀብትን ጥቅም ላይ በማዋል የኢኮኖሚ ምንጭ ሆኖ የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት እንዲችል በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡

ለአገሪቷ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ይታወቅ የነበረው ወርቅ ባለፉት ዓመታት ከሕገወጥ ወርቅ ማምረትና ግብይት ጋር በተያያዘ ለብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን መቀነሱ ይታወቃል፡፡ የወርቅ ምርቱ በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጪ ሀገሮች ይወሰድም ነበር፡፡ መንግስት ይህን ሕገወጥ ድርጊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል አቋቁሞ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህም በርካታ ሕገወጦች በቁጥጥር ስር ውለውም እንደነበር ይታወሳል፡፡ በድርጊቱ የተጠረጠሩ የውጭ ዜጎች ላይም ጭምር እርምጃ እንደተወሰደባቸውም ይታወቃል፡፡

የብሔራዊ ባንክ መረጃ እንደሚያመላክተው፣ የወርቅ ምርት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ የኤክስፖርት ምርቶች መካከል አንዱ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ለውጭ ገበያ ከሚላክ ወርቅ ብቻ ከ600 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ይገኝ ነበር፤ በ2014 ዓ.ም ከወርቅ ብቻ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ 672 ሚሊዮን ዶላር ደርሶም ነበር፡፡

ይህ ወርቅ የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሬ እየቀነሰ መጥቶ አነጋጋሪ እስከ መሆን ደርሷል፡፡ የወርቅ ክምችቱ ሳይኖር ወይም ሳይመረት ቀርቶ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች የወርቅ ሀብቱ ለብሔራዊ ባንክ እንዳይደርስ በመደረጉ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይም ወርቅ ለኮንትሮባንድ ንግድና በሕገወጥ ግብይትና ዝውውር የተጋለጠ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እምብዛም ውጤት ሳያስገኝ ዓመታት አልፈዋል፡፡

ለእዚህ ምክንያት ከተባሉት መካከል ብሔራዊ ባንክ ለወርቅ አቅራቢዎች የሚሰጠው ክፍያ አማላይ አለመሆኑና የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ሁኔታም ብሔራዊ ባንክ ለአቅራቢዎቹ የሚሰጠውን ዋጋ በየጊዜው እያሻሻለ እንዲሄድ አርጎት ቆይቷል፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን የሚመረተው ወርቅ ሕገወጦች እጅ በመውደቁ ለባንኩ የሚገባው ወርቅ መጠን ሲያሽቆለቁል ቆይቷል፡፡

በተለይ ወርቅ አምራች በሆኑት ክልሎች በቤኒሻንጉል፣ በጋምቤላ እና በትግራይ ክልል ሕገወጥነት ተንሰራፍቶ ወርቅ አግባብ ባልሆነ መልኩ ግብይት ሲካሄድበት ከመቆየቱም ባሻገር በኮንትሮባንድ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ይወጣም ነበር፡፡

በመንግሥት በኩል ኮንትሮባንድ ንግድና ሕገወጥ ዝውውር ለመከላከል የጸጥታ አካላት ያካተተ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ሥራዎች ሲሰሩና ክትትል ሲደረግ ቢቆይም፣ በክልሎች እየጨመረ የመጣው የወርቅና የማዕድናት ኮንትሮባንድ ንግድን ማስቆም ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት መንግሥት በማዕድን ዘርፍ በተለይ በወርቅ ልማትና ግብይት ላይ የገጠመውን ችግር ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ማዕድን አምራቾችና አዘዋዋሪዎች ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በሕገወጦች ላይ እርምጃ በመውሰድና የተለያዩ ማሻሻያዎች በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከወራት በፊት ደግሞ ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው የታመነበት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሙሉ ትግበራ መግባቱ ይታወሳል፡፡ ይህ ለወጪ ንግዱ፣ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት መጨመር፣ ወዘተ ከፍተኛ ፋይዳለው ይታወቃል፡፡ ማሻሻያውን ተከትሎ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ስርዓት ማሻሻያ አድርጓል፡፡ ይህም የውጭ ምንዛሬ ግብይቱ ከብሔራዊ ባንክ ውጪ እንዲከናወን ወይም በገበያ እንዲመራ የሚያስችል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ግብይት ላይ ያደረገው ማሻሻያ ለወርቅ አቅራቢዎች ዘላቂ ማበረታቻ እንደሚፈጥር በመታመኑ እና የወርቅ አቅርቦትን በዘላቂነት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተሻሻለ መመሪያ ማውጣቱ ይታወሳል፡፡ ባንኩ የወርቅ ዋጋን አስመልክቶ ከሐምሌ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ በዋለው አሰራር መሰረት የወርቅ መግዣ ዋጋ ባንኩ ድረ-ገፅ ላይ በየዕለቱ በሚገለጸው የውጭ ምንዛሪ መሸጫ ተመን ላይ ተመስርቶ የሚወሰን እንደሆነ መግለጹ ይታወሳል፡፡

መንግሥት እየወሰዳቸው ያሉት እነዚህን መሰል ማሻሻያዎች ደግሞ ወደ ባንኩ በሚገባው የወርቅ መጠን ላይ ለውጦች እንዲታዩ እያደረጉ ስለመሆናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 100 ቀናት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት በተገመገመበት ወቅት የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፣ በተያዘው በጀት ዓመት የስምንት ነጥብ አራት በመቶ እድገት የማስመዝገብ ውጥን ተይዟል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 100 ቀናት ተግባራዊ የተደረገው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተሻለ የኢኮኖሚ አፈጻጸም በወጪ ንግድ፣ በመንግሥት ገቢ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በውጭ ምንዛሪ ግኝት የተሻለ አፈጻጸም ተመዝግቧል። ከወጪ ንግድ አንጻር በተለይ በወርቅ ወጪ ንግድ እጅግ ስኬታማ ሥራ መከናወኑን አብራርተዋል።

ለአብነትም በ2016 በጀት ዓመት ዓመቱን ሙሉ ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን አራት ቶን ብቻ እንደነበር የተናገሩት ሚኒስትሯ፣ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሶስት ወራት ብቻ ሰባት ቶን ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባቱን ተናግረዋል። ይህም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማምጣቱን አመላካች ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡

ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደ ሚያመላክተው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በራሱ ለውጥ ማምጣት ችሏል፡፡ የማዕድን ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲያስ እንዳሉት፣ መንግሥት ተግባራዊ እያደረገው የሚገኘው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የማዕድናት ምርታማነትን በተለይ የወርቅ ምርትን በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በአነስተኛ ደረጃ ይመረት የነበረው የማዕድን ምርት በከፍተኛ መጠን እያሳደገው ነው፡፡

የማእድን ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ እንዳሉትም፣ ማሻሻያውን ምክንያት በማድረግ በተያዘው በጀት ዓመት ስምንት ነጥብ ስድስት ቶን ወርቅ ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት /ባለፉት ሶስት ወራት/ ብቻ የእቅዱን 70 በመቶ ማሳካት መቻሉን አስታውቀዋል፤ ማሻሻያው የማዕድናት አምራቾችን ተጠቃሚ እያደረጋቸው በመሆኑ የተሻሉ ማሽነሪዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ገዝተው ወደ ምርት ሂደቱ እየገቡ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የባሕላዊ አምራቾች ካፒታላቸውን በማጠራቀም ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ፣ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ፣ ገቢያቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ምርትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በተያዘው በጀት ዓመትም ለማምረት ከታቀደው ስምንት ነጥብ ስድስት ቶን ወርቅ ሶስት ሺህ 600 ኪሎ ግራም ያህል ወርቅ በባሕላዊ መንገድ የሚመረተው ሲሆን፣ የባሕላዊ የማዕድን ቁፋሮ ወደ አነስተኛና መካከለኛ እንዲሁም ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ባሕላዊ የማዕድን አመራረት ዘዴ ከፍተኛ የሆነ የምርትና የጉልበት ብክነት እንዳለው ጠቅሰው፣ የምርትና የጉልበት ብክነትን ለመቀነስ አመራረቱን የማዘመን ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አስታወቀዋል፡፡

በክልል ደረጃም ወርቅ ለማምረት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ጥረቶች እየተደረጉ ለውጦችም እየታዩ ስለመሆናቸው ይገልጸል፡፡ ለአብነትም የትግራይ ክልል ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ሕገወጥነት በተስፋፋበት የወርቅ ምርት ላይ በተደረገው ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ ብሔራዊ ባንክ ባደረገው የወርቅ መግዣ ተመን የተነሳ በዓመቱ መጨረሻ ወራት ጀምሮ አበረታች ለውጦች እየታየ መሆኑን የክልሉ መሬት አጠቃቀም አስተዳደርና ማዕድን ቢሮ መረጃ ያመላክታል፡፡

ክልሉ በ2016 በጀት ዓመት ወርቅ በማምረት 50 ኪሎ ግራም ወርቅ ለማስገባት አቅዶ፤ በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ባሉ ሦስት ወራት እቅዱን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት ችሏል፡፡ ይህ የሆነበት ዋንኛ ምክንያት በተሰራው ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ሥራ በተለይ ወርቅ ላይ ትኩረት መሰጠቱ በዓመቱ መጨረሻም የተያዘውን እቅድ ማሳካት ተችሏል፡፡ በባለፈው ዓመት ማገባደጃ ሦስት ወራት የወርቅ ምርት በሕጋዊ መንገድ ወደ ብሔራዊ ባንክ የመግባት ሁኔታ በመነሻነት የተያዘና ይህንን እቅድ ሊያሳካ የሚያስችል መሆኑ ተመላክቷል፡፡

በክልሉ በተያዘው 2017 በጀት ዓመት 800 ኪሎ ግራም ወርቅ ገቢ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡ ይህም 700 ኪሎ ግራም ወርቅ በኢዛና ድርጅት (ኢዛና ሕጋዊ የሆነ ወርቅን ከአምራቾች ተረክቦ ለብሔራዊ ባንክ የሚያስገባ ነው) አማካኝነት የሚገባ ሲሆን፤ 100 ኪሎ ግራም ከባሕላዊ አምራቾች ገቢ እንዲደረግ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ አሁን ላይ በወርቅ ምርት ላይ ለውጦች እየተመዘገቡ ስለመሆናቸው ወደ ብሔራዊ ባንክ እየገባ ያለው የወርቅ መጠንና ለውጪ ገበያ ቀርቦ ያስገኘው ከ500 ሚሊየን ዶላር በላይ ያመለክታል፡፡ በተለይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ውጤቶች እየተመዘገቡ ናቸው፡፡ በዚህ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የወርቅ መጠን ባለፈው ዓመት ዓመቱን በሙሉ ከተገኘው ውጤት ሁለት እጥፍ ሊሆን ትንሽ የቀረው መሆኑም ይህንኑ ያመለክታል፡፡

እንደ ሀገር በወርቅ ግብይት ላይ እየታየ ያለው ለውጥ ሀገሪቱ ከወራት በፊት ተግባራዊ ያደረገችው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያና እሱን ተከትሎ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ስርዓት ማሻሻያ አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ሀገሪቱ ካላት እምቅ የወርቅ ማእድንና በባሕላዊና በዘመናዊ መንገድ እየለማ ካለው የወርቅ ሀብት ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ የማሻሻያው ትግበራ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፤ ማሻሻያው ገና ወደ ትግበራ እንደገባ ትልቅ ውጤት ማየት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት በቀጣይም ሰፊ ለውጥ መመዝገብ እንደሚችልም ያመላክታል፡፡

ይህን ውጤት ዘላቂ ለማድረግ በማሻሻያው ትግበራ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ወርቅን ሲፈጸምበት ከቆው ሕገወጥ ተግባር ለመታደግ የተጀመረውን ጥረት ውጤታማ ማድረግም ይቻላል፡፡ ወርቅ በዚህ ልክ ዋጋ እያወጣ ከመጣ አምራቾች ለሕገወጦች ከማቅረብ ይልቅ ለብሔራዊ ባንክ ለማቅረብ ይነሳሳሉ፤ በዚህም ሀገር ከወርቅ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ እየጨመረ ይመጣል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ያዘው..ሌባ ሌባ..

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)**

አርብ ከሰአት የተቋሙ ጸሀፊ የሆነች ሴት ደውላ ፈተናውን በአንደኝነት አልፈሀል ሰኞ ለቃለመጠይቅ ትፈለጋለህ ካለችኝ ሰአት ጀምሮ ምድር ጠባኝ ነው የሰነበትኩት፡፡ ቅዳሜና እሁድ እንደ ዝንተዓለም በላዬ ላይ ሲያልፉ ደህና ግቡ ከሚል ምርቃት ጋር ነበር፡፡ ጊዜም እንደመንገደኛ ስንቅ ቋጥሮ ወደሩቅ ሀገር የሚሄድ የሚመስልበት አንዳንድ ኩነት አለ... ቅዳሜና እሁድ ከነጓዛቸው ወደሰኞና ማክሰኞ ወደድሮም ሲያዘግሙ እንዲያ ነበር የመሰሉኝ፡፡

ሰኞ ጠዋት ከዚህ በፊት እንዳሳለፍኳቸው ማለዳዎች አልመስልህ ብሎኝ ነበር፡፡ በፍኖ ቶሎዛ ያንቀላፋው ያዕቆብ እንኳን የኔን አይነት የተዋበ ሌሊት ስለማሳለፉ እጠራጠራለሁ። የሚረፍድብኝ መስሎኝ ቁርሴን ዘልዬ ነጭ ሸሚዝ ከጥቁር የጨርቅ ሱሪ ጋር ለብሼ ከቤት ወጣሁ፡፡

..ቤታችን ለባቡር ጣቢያ አቅራቢያ ነው፡፡ በግምት ሀያ ሰላሳ ርምጃዎች፡፡ ትኬት ቆርጦ ባቡር የመሳፈርን ያክል የሚቀለኝ የለም፡፡ ሰአቴን አየሁ..ታክሲ በማጣት ሩብ ደቂቃዎች አልፈዋል። እስከቅንድቡ የተሞላ ባቡር አጠገቤ መጥቶ ቆመ፡፡ ምን ላይ ሊቆም እንደሆነ ባላውቅም ሰው እየተፈራረጠ ይሄዳል፡፡ እዚህስ አልገባም ስል አሳለፍኩት፡፡ ከዛ በኋላ የሞሉ ሶስት ታክሲዎች አለፉኝ፡፡ አስር ደቂቃዎች ተቆጠሩ..ልቤ ከቅድሙ ሩብ ጋር ደባለቃቸው፡፡ ከርቀት የባቡር ድምጽ ተሰማኝ ምንም ይሁን በዚህ መሄድ አለብኝ እያልኩ ሳስብ ከቅድሙ በባሰ ሞልቶ አጠገቤ በሩን ከፈተ፡፡ ላልሄድበት በማልኩት ባቡር ልሄድ ግድ ሆነብኝ። የጋለ ትኩስ ትንፋሽ ከሆነ አይነት ጠረን ጋር እንኳን ደህና መጣህ አለኝ። እግሬ ስፍራ አግኝቶ ስለመቆሙ እጠራጠራለሁ። ትፍፍጉ፣ ጥግግቱ ክፉ መከራን ያስንቃል፡፡ ሲኦል የገባሁ ነበር የመሰለኝ፡፡ ድህነት ሲኦል አይደል? ያለው ብሆን ኖሮ በኮንትራት ታክሲ ከጉዳዬ ደርሼ ነበር፣ ውስጤን በብሶት እንዲህ አመስኩ፡፡

የሆነ ፌርማታ ላይ አንድ ሴት ልትወርድ የቡጢ ያህል ወገቤን ደቁሳኝ ወደበሩ ተሽጋገረች፡፡ ብዙ ቦታ ይዛ አጠገቤ የቆመች እንደሆነ የገባኝ ከአጠገቤ ስትሸሽ ነበር፡፡ አርበ ሰፊ ናት.. ለብቻዋ የያዘችው ቦታ የእኔን ያህል ሃምሳ ያቆማል ስል በውስጤ ቀለድኩ፡፡ የእሷን መውረድ ተከትሎ አጠገቤ የሆነ እሪታ ተሰማ፡፡

‹ሀብሌን..ሀብሌን..ዘረፈኝ!

‹ዘረፈኝ..ዘረፈኝ..እሱ ነው ያዙት› ስትል ያለሁበትን ፈነቃቅላ ውጪ ወደሚታዩት ፖሊሶች ጮኸች፡፡

ሁሉም በየግሉ የራሱን አጉተመተመ፡፡

‹ማን ይሆን የፈረደበት? አለ ውስጤ፡፡ በዚህ ሌባ አማካኝነት ከጉዳዬ ላረፍድ እንደሆነ ሳውቅ ሌባ በተባለው ቀማኛ ላይ አንድ ሁለት ቡጢ ማዋጣት እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ የጅህን ይስጥህ..ወዴት እየሄድኩ እንደሆነ ሳታውቅ እንዴት በዚ ሰአት ትዘርፋለህ..? የእኔን መሳይ በእድሜ ለአንድ ጊዜ የሚመጣ እድል ይዘው ወደጉዳያቸው እየሄዱ ያሉ ሰዎች እንዳሉ ብታውቅ በስራህ ታፍር ነበር ስል ጥርሴን ነከስኩበት፡፡

ተሰረቀብኝ ያለችው ሴት በጩኸትና በለቅሶ ከባቡሩ ወርዳ ወደእኔ እያመላከተች ‹ያዙት..እሱ ነው ሌባው..ያዙት› ስትል ጮኸች፡፡ ሌላ ሰው ማለቷ ነው ብዬ ሰው ፍለጋ ወደ ኋላዬ ስገላመጥ..ምን ትገላመጣለህ..? ያዙት..ሰርቆኛል› ስትል እሪ አለች። ምን እያሰብኩ እንደሆነ ሳላውቅ ሁለት ወጠምሻ ፖሊሶች ግራና ቀኝ በሀይል ጎትተው ከባቡሩ አወጡኝ፡፡ ጉተታቸውን መቋቋም ስላልቻልኩ መሬት ላይ በሀይል ወደኩ፡፡

በሁለቱ ፖሊሶች ግራና ቀኝ ተይዤ ወደፖሊስ ጣቢያ ተወሰድኩ፡፡ ሲሰርቅ እጅ ከፍንጅ የተያዘ ሌባ ነው ሲሉ ለመርማሪ ፖሊስ አስረከቡኝ፡፡ አልቃሿ ሴት ‹ሀብሌን ከአንገቴ ላይ...› ሳትጨርሰው ለቅሶዋ አስቆማት፡፡ በአልቃሿ እዬዬ መሀል በአራት እና በአምስት ፖሊሶች ተከብቤ ተብጠለጠልኩ፡፡

መርማሪው ፖሊስ ‹ና ወደዚህ! ሲል አንድ ጊዜ ፊቴ ላይ በጥፊ ደረገመብኝ፡፡ ‹ሰርተህ አትበላም ከምትዘርፍ?

ዝም አልኩ..አንድ እውነት ሲኖራችሁ በከሳሾቻችሁ ፊት ዝምታ ነው መልሳችሁ፡፡ እየሱስ በፍርድ አደባባይ፣ በጲላጦስ ፊት ለምን ዝም እንዳለ፣ ስቀለው.. ስቀለው በሚሉ የከፋት ድምጾች ፊት ለምን እንዳቀረቀረ አሁን ገባኝ፡፡ እስካልደረሱብን ድረስ ሌሎች ላይ አይተናቸው የሚገቡን ነገሮች ጥቂቶች ናቸው፡፡

‹የታል ሀብሉ? መርማሪው ፖሊስ በጎላ ድምጽ ጠየቀኝ፡፡

‹እኔ ምንም አልሰረኩም..›

ሁለተኛውን ጥፊ አስከተለ፡፡ ተንገዳገድኩ..ለረጅም ሰአት አዞረኝ፡፡ ገጼ ላይ የመዳፉ ሰንበር የአምስት ጣቶቹን ታርጋ ይዞ ይታኛል፡፡ እስከዛሬ እንዲህ ተመትቼ አላውቅም፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ሲባልም ይሄን እንደሚመስልም አላውቅም ነበር፡፡ እኔ የተማርኩት አንድ ሰው ወንጀል ቢሰራ እንኳን በህግ እንደሚዳኝ እና ማንም በአካሉ ላይ ጥቃት እንደማያደርስበት ነው፡፡ እኔ የማውቀው አይደለም ያልሰረቀ ሲሰርቅ የተያዘም ቢሆን በህገመንግስቱ መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆን ነው፡፡

‹ልብሱን አውልቃችሁ ፈትሹት..› አለ

ልብሴን አውልቀው ፈተሹኝ፡፡ ሀብሉን ያስቀምጥበታል ብለው ያሰቡበትን ሁሉ እርግጠኛ በሆነ መንገድ ፈተሹት፡፡ ምንም አላገኙም፡፡

‹ዝም ያለው ምናልባት አፉ ውስጥ አድርጎት ሊሆን ይችላል.. ከማለቱ አንዱ ፖሊስ ‹እስኪ አፍህን ክፈት? ሲል ተጠጋኝ፡፡ አፍ ይሄን ያክል ሰፊ ነው? የሆነ ጓዳ ጎድጓዳ ያለው ይመስል ለረጅም ሰአት ሲያስተውለው ነበር፡፡

‹የት ነው ያደረከው ሀብሉን? እውነቱን ብትናገር ይሻልሀል ያለዛ? አለኝ ሁለት ጥፊ ያላሰኝ መርማሪ፡፡

‹የሌባ ነገር ምንድነው እሱ..? አምጣው! አለኝ በካኪ ወደተሸፈነው ዶክመንቴ እያየ፡፡ እስክሰጠው ሳይጠብቅ ከእጄ ላይ መንጭቆ ዶክመንቴን ከመሬት ዘረገፈው፡፡ ‹እሄኔ ገንዘብ መስሎት ከአንዱ ከርታታ ላይ ቀምቶት ነው› አለ ይዘውኝ ከመጡት ፖሊሶች አንዱ፡፡ እንደተራ ነገር ቆሻሻ ላይ እያንደባለሉ አገላበጡት፡፡ ከስምንተኛ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ያሉ የትምህርት ማስረጃዎች ለአንድ ኢትዮጵያዊ ምን ማለት እንደሆኑ ላልገባው የህግ አስከባሪ ሊቅነት ምን ይሰራል? የነፍሴ ጥያቄ ነበር፡፡

መሬት ከወደቁ የትምህርት ማስረጃዎቼ መሀል ስትሬት ፎር ያመጣሁበት የአስረኛ ክፍል የማትሪክ ውጤቴና ሜዳሊያ የተሸለምኩበት የዩኒቨርሲቲ ወረቀቴ ደረታቸውን ገልጠው አይኔ ውስጥ ተማገዱ፡፡ ለምን እንደሆነ በማላውቀው ሁኔታ አይኖቼ እንባ አቀረሩ፡፡

ከወረቀቱ ጋር አብሮ የወደቀ ሀብል እንደሌለ ሲያውቅ ‹ቆሻሻህን አንሳ› ሲል ገላመጠኝ፡፡ ቆሻሻ እንዳይደለ ልነገርው ባልፈልግም አለመንገር ግን አልሆነልኝም ‹ቆሻሻ ነፍስ ያለው የብርሀንን ውበት ሊረዳ አይችልም› ስል ለሶስተኛ ጥፊ የዳረገኝን ንግግር አደረኩ፡፡ ሶስተኛው ጥፊ ፊቴ ላይ ሲያርፍ ከደም ጋር ነበር፡፡ እንደጦስ ዶሮ አንደፋድፎኝ፡፡ ብቻውን የመታኝ አልመሰለኝም..የወዳጆቹን መዳፍ አስተባብሮ ያሳረፈብኝ እንጂ፡፡ የአንድ ሰው መዳፍ ይሄን ያህል ሰማይ ከምድር ያዞራል?

በሆነ የዛለ አቅም ሜዳ የተበተነ ወረቀቴን ላነሳ ጎንበስ ባልኩበት ቅጽበት በመካከላቸው አብሯቸው ሆኖ ሲናገር ያላየሁት አንድ ፖሊስ ወደወረቀቴ ጎንበስ ብሎ ኖሮ ቀድሞኝ የዩኒቨርሲቲ ውጤቴን በእጁ አስገባው፡፡ ያመጣሁት ውጤት ፊቱ ላይ አንዳች ስሜትን ሲጭር እያየሁ ነበር፡፡ ቀና ብሎ አስተዋለኝ..በወፋፍራም ጥፊዎች ዝዬ ደከሜበት ነበር፡፡ እኔጋም እሱጋም ያሉትን ወረቀቶች አስተካክሎ ካኪው ውስጥ አስገብቶ አቀበለኝ፡፡

ተሰረቀብኝ ያለችው ሴት ካላባራ ለቅሶ ጋር ከአሁን አሁን ፍርዴን በመጠባበቅ ቆማለች፡፡ ጉንጮቿ በእንባ ቦይ ሰንበር አበጅተዋል...፡፡ ከበዋት የቆሙትም ፖሊሶች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እርስ በርስ በመጠያየቅ ይታዩኛል፡፡ አይኔን ወደእጅ ሰአቴ ሰደድኩ..ስድስት ሰአት ከነግርማው አላገጠብኝ። ከእለታት ውስጥ የበቀለ ህልሜ በህልም እልም ሰወረኝ፡፡ ይሄን ነው በህይወት ማርፈድ የምለው፡፡ ይሄ እኮ ነው ትንሳዔና ሞት በአንድ ገጽ ላይ፡፡ ከዚህ ለማምለጥ እኮ ነው ሞቴን አሳምርልኝ የምንለው። ለዚህ እኮ ነው በሰላም አውለኝ የሚጠቅመው፡፡

ጥሩ የመሰለኝ ፖሊስ ወደሴትዮዋ እያየ ‹እርግጠኛ ነሽ እሱ ነው የሰረቀሽ?

‹አዎ እሱ ነው የሰረቀኝ..ሲነካካኝ፣ ሲላፋኝ ከአንዴም ሁለት ጊዜ አይቼዋለሁ› አለች በእርግጠኝነት፡፡

‹ምናልባት ወልቆ አሊያም ተበጥሶ ወደጉያሽ ገብቶ ሊሆን ይችላል..ግፊያ ካለ እንደዛ አይነት ነገር ይከሰታል› አለ፡፡

‹እረ በፍጹም እሱ ነው የወሰደው..› በማለት እየተናገረች እጇን ወደጉያዋ ሰደደች..እጇን ስታወጣው ግን ከሀብሏ ጋር ነበር።

‹ክው አለች.. ሁሉም ፖሊሶች ስሜቷን ተጋሯት፡፡ አንዴ ሀብሉን አንዴ ፖሊሶቹን እያየች ደርቃ ቀረች፡፡ ምንም ያለ ማንም አልነበረም፡፡ ነጻ መውጣቴን ሳውቅ ትቻቸው ወጣሁ.. ከኋላዬ አንድ ኮቴ ይሰማኛል..አልዞርኩም...ማንም ቢሆን ግድ አልነበረኝም፡፡ እየፈጠንኩ ነው..ወዴትና ለምን እንደምፈጥን አላውቅም፡፡ ግን ከህይወት፣ ከሰውነት መራቅ አምሮኛል.. የምደርስበት ሌላ ዓለም ናፍቆኛል፡፡

‹ፍሰሀ› አለኝ የሆነ ድምጽ

ወደ ኋላዬ ዞርኩ..ሲተባበረኝ የነበረው ፖሊስ ‹መታወቂያ ጥለሀል› ሲል ወደቆምኩበት ተረማምዶ አቀበለኝ፡፡ ትቼው ሄድኩ። ቆሞ እያየኝ እንደሆነ ያወኩት በኮቴው ነው..በማይሰማ ኮቴው፡፡

ከየት እንደቀረሁ..ከየት እንደዘገየሁ...ምን እንደቀረብኝ..ከምን እንዳስመለጡኝ ማንም አያውቅም፡፡ ወዴት እየሄድን እንደሆነ.. ለምን እየሄድን እንደሆነ አያውቁም፡፡ አንዳንዶች በአሁን ውስጥ ዘላለምን ይነጥቁናል፡፡ በቅጽበት ውስጥ ሁልጊዜን ያሳጡናል.. በዛሬ ነገን ይቀሙናል፡፡ ደስ ከሚል አሁን ደስ ወደማይል በኋላ እንደገፈተሩኝ ቢያውቁ ተመኘሁ..ባያውቁም ግድ የለም፡፡

# ዓለም አቀፍ

## አውስትራሊያ ከ16 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ማኅበራዊ ሚዲያን ልታግድ ነው

የአውስትራሊያ መንግሥት ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት የትኛውንም ማኅበራዊ ሚዲያ እንዳይጠቀሙ የሚያግድ ሕግ ሊያወጣ ነው። ለሀገሪቱ ፓርላማ በሚቀጥለው ሳምንት የሚቀርበው ረቂቅ ሕግ ማኅበራዊ ሚዲያ በአውስትራሊያ ህጻናት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት “ለመከላከል” ያለመ እንደሆነ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አንቶኒ አልባኔዝ ተናግረዋል።

“ይህ ሕግ ለአባቶች እና ለእናቶች ነው። እንደእኔ ወላጆች በኢንተርኔት ላይ የልጆቻችን ደኅንነት አሳምሞናል። የአውስትራሊያ መንግሥት በዚህ ሕግ ከጀርባችሁ ነኝ እያለ ነው” ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል። የረቂቅ ሕጉ ዝርዝር ለፓርላማ ቀርቦ ክርክር የሚደረግበት ቢሆንም እገዳው ቀድሞውኑ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ባሉ ታዳጊዎች ላይ እንደማይተገበር መንግሥት አስታውቋል።



ሆኖም ወላጆች ፍቃድ ቢሰጧቸውም ከተጠቀሰው ዕድሜ በታች ያሉ ህጻናት ማህበራዊ ሚዲያን መጠቀም አይችሉም። ህጻናቱ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን እንዳይጠቀሙ ለመከላከል ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ የማኅበራዊ ሚዲያ ባለቤቶች ኃላፊነት እንደሚሆንም መንግሥት አስረድቷል።

አልባኔዝ በህጻናቱ ተጠቃሚዎች ላይ ምንም ዓይነት ቅጣት አይኖርም ቢሉም ሕጎቹን ማስከበር የአውስትራሊያ የኢንተርኔት ተቆጣጣሪ ኢ-ሴፍቲ ኮሚሽነር እንደሚሆን ገልጸዋል። ይህ ታዳጊዎችን ከማኅበራዊ ሚዲያ የሚያግደው ሕግ ከጸደቀ ከ12 ወራት በኋላ ተግባራዊ ይሆናል የተባለ ሲሆን፣ በየጊዜውም ግምገማ ይደረግበታል ተብሏል።

አብዛኞቹ ባለሙያዎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች የታዳጊዎችን አዕምሯዊ ጤንነት ሊጎዱ እንደሚችሉ ቢስማሙም ሙሉ በሙሉ ይታገድ በሚለው ላይ ተከፋፍለዋል። አንዳንዶች እገዳዎች ውስብስብ የሆነውን የኢንተርኔት ዓለም እንዴት ማሰስ እንደሚችሉ ከማስተማር ይልቅ እንደ ቲክቶክ፣ ኢንስታግራም እና ፌስቡክ ላሉ መተግበሪያዎች ያላቸውን ተጋላጭነት የሚያዘገይ እንደሆነ ይተቻሉ።

ቀደም ሲል የአውሮፓ ኅብረትን ጨምሮ ህጻናትን ከማኅበራዊ ሚዲያ ለመገደብ የተደረጉ ሙከራዎች አልተሳኩም ወይም አተገባበራቸው ፈታኝ ሆኗል። ለዚህም ደግሞ አንደኛው ምክንያት የዕድሜ ማረጋገጫ መስፈርቶችን ሊያሳልፉ የሚችሉ መተግበሪያዎች በመኖራቸው ነው።

መንግሥት ያቀደውን እገዳ በሀገሪቱ ካሉ የህጻናት መብት ተሟጋች ቡድኖች ትልቁ የሆነው የአውስትራሊያው የህጻናት መብቶች ግብረ ኃይል ተችቶታል። ግብረ ኃይሉ ከ100 በላይ ምሁራን እና 20 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የፈረሙበት ግልጽ ደብዳቤ ለመንግሥት ያስገባ ሲሆን፣ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን ከማገድ ይልቅ “የደኅንነት መመሪያዎችን” እንዲያስተዋውቁ ጠይቋል።

ቡድኑ በተጨማሪም ኢንተርኔትን ለመቆጣጠር የተነደፉ “ብሔራዊ ፖሊሲዎች” ህጻናት የዲጂታል ከባቢያቸው ጋር እንዲገናኙ እና ደኅንነቱ በተጠበቀ መልኩ መረጃዎችን እንዲያገኙ ዕድል መስጠት መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ምክርን ጠቁሟል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## እስራኤል ከአሜሪካ 25 “ኤፍ-15” የውጊያ ጄቶችን ልትገዛ ነው

እስራኤል በአሜሪካ ድጋፍ የቀጣዩ ትውልድ “ኤፍ-15” ተዋጊ ጄት ባለቤት ለመሆን ተቃርባለች። የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር 25 “ኤፍ -15” ጄቶችን ለመግዛት ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ስምምነት መፈራረሙን አስታውቋል።የቦይንግ ዘመኑን የዋጁትና የቀጣዩ ትውልድ “ኤፍ-15ጄቶች” “ኤፍ-15ኢኤክስ” የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል።

5 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡት ጄቶች ግዥ የአሜሪካ ኮንግረንስ በዚህ አመት ለእስራኤል ያጸደቀው ድጋፍ አካል መሆኑንም ሚኒስቴሩ በኤክስ (ትዊተር) ገጹ ላይ ባሰፈረው ጽሁፍ አመላክቷል።የጦር ጄቶቹ የእስራኤል የአየር ሃይል በመካከለኛው ምስራቅ ቀዳሚነቱን ያስቀጥላሉ የተባለ ሲሆን፤ አሁንም ሆነ ወደፊት በቀጣናው ለሚገጥሙ ችግሮች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት እንደሚያግዙም ተገልጿል።



የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው፤ ቦይንግ “ኤፍ -15” ጄቶቹን ለእስራኤል ከ2031 ጀምሮ ማቅረብ ይጀምራል፤ በየአመቱም ከአራት እስከ ስድስት ጄቶችን አጠናቆ ያስረክባል። “ኤፍ-15 ጄቶቹ በዚህ አመት ከገዛናቸውና (በሊባኖስና ጋዛ) ጦርነት ውጤታማነታቸውን ካሳዩን ኤፍ-35 ጄቶች ጋር ሲጣመሩ የእስራኤልን የአየር ሃይል አቅምና ተደራሽነት ይበልጥ ያጠናክሩታል” ብለዋል የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር ዋና ዳይሬክተር ኢያል ዛሚር።

የቦይንግ “ኤፍ-15” ጄቶች (“ኤፍ-15ኢኤክስ”) በሚሸከሙት ክብደት፣ በሚያካልሉት ርቀትና በፍጥነታቸው የዘመኑ የመጨረሻ ቴክኖሎጂ ውጤት ናቸው ተብሏል። ለየትኛውም የውጊያ አውሮፕላን ሽፋን የሚሰጡ የጀርባ አጥንት ይሆናሉም ነው ያለው ቦይንግ በድረገጹ ባሰፈረው መግለጫ።

ኤፍ-15 ኢኤክስ”እስከ 13 ሺህ 300 ኪሎግራም የሚመዝኑ የጦር መሳሪያዎችን የሚይዝ፤12 መካከለኛ ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤሎችን እንደሚሸከም፤በሰአት 3 ሺህ 581 ኪሎ ሜትሮችን እንደሚጓዝ፤ ዘመናዊ ራዳር፣ ሴንሰሮች እና የኮሙዩኒኬሽን መሳሪያዎች የተገጠሙለት መሆኑን ጠቅሶ አል ዐይን ዘግቧል፡፡

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን- አሳውን ሳይሆን አጠማመዱን

ዳግም ከበደ

**ለስልጠናው የተመረጡት ነዋሪዎች ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ በቀጥታ ወደ ስራው እንዲገቡ የሚያስችል የፋይናንስ አቅርቦት ፋውንዴሽኑ ከመንግስት ጋር በመተባበር ይመቻችላቸዋል፡፡ በዚህም 20 በመቶ የሚሆነውን የጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ሲሰጥ ቀሪውን 80 በመቶ ደግሞ ሰልጣኞቹን ከመንግስት አበዳሪ ተቋማት ጋር በማገናኘት በብድር እንዲወስዱ ይደረጋል**

ኢትዮጵያውያን በጠንካራ ማኅበራዊ ትስስር፣ የአብሮነትና የመደጋገፍ ባሕል ይታወቃሉ። ማሕበራዊ ትስስራቸው አገር በቀል እውቀትን፣ ባሕልና ማንነትን ማዕከል ያደርጋል። ይህ ጠንካራ ማሕበራዊ ውል በጋራ ከመኖር ያለፈ ትርጉም አለው። ተደጋግፎ የመኖር (የአንቺ ትብሽ አንተ ትብስ መባባል) ከጥንትም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የነበረ ነው። ይህ ባሕላዊ መሰረት ያለው እሴት የዜጎች ማሕበራዊ መጠንከር አንዱ ምሳሌ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በተለያየ ምክንያት የተቸገሩ ዜጎች፣ ግለሰቦችና የማሕበረሰቡን አባላት በተደራጀ መንገድ (በእቁብ፣ እድርና በሌሎች አደረጃጀቶች) የመደገፍና የማቋቋም ልምድ አለ። ይህ ስርዓት ከሌላው ዓለም በተለየ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በብዛት ይንጸባረቃል።

ለምሳሌ በጉራጌ ብሔረሰብ ቤተሰብ፣ ወዳጅ እና የልብ ጓደኛን በእቁብና በመዋጮ በመደገፍ የንግድ ስራ እንዲጀምር፤ ድጋፉን ያገኘው ግለሰብ ሰርቶና ተለውጦ እሱ ደግሞ በምላሹ ሌሎችን በተመሳሳይ እንዲያግዝ የሚያደርግ የቆየ ባሕል አለ። በኦሮሞ ብሔረሰብም እንዲሁ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ ሀብት ንብረቱን ያጣ ግለሰብና ቤተሰብን ፈጥኖ በመድረስ የማገዝ ልምድ አለ። በሌሎች በርካታ ኢትዮጵያውያንና ብሔረሰቦች ዘንድ በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች የመደጋገፍና የመተባበር እሴት ይታያል።

በኢትዮጵያ ከላይ ካነሳናቸው መንገዶች ሌላም የበጎ አድራጎት ተግባር በተለያየ መልኩ ይከወናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማሕበራዊ ሚዲያን ለበጎ ዓላማ የሚያውሉ (ጥቂት በመደጋገፍ ስም የሚነግዱ ወንጀለኞች ቢኖሩም) እየበረከቱ ነው። ከዚህ ባሻገር አገር በቀል የግብረ ሰናይ ድርጅት በመክፈት በጎ ፍቃደኞችን በማስተባበር በዘላቂነት ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን «አለሁ» የማለትና ለወጣቶች፣ ሴቶችና ሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች የስራ እድል መፍጠር እየተለመደ ነው። ይህ መሰሉ ስርዓት ባሕላዊውን አደረጃጀት የሚያጠናክር የቆዩ እሴቶችን በዘላቂነት ለማስቀጠል የሚረዳ እንደሆነ ይታመናል።

በባሕላዊ መንገድና በተቋማዊ አደረጃጀት ከሚደረጉ የበጎ ስራ ተግባራት ባሻገር ግለሰብ ተፅእኖ ፈጣሪዎችም እንዲሁ በዚህ ተግባር ላይ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ይታመናል። በግል ጥረት፣ ሀብትና እውቀታቸው የበርካታ ዜጎችን ሕይወት ሲያሻሽሉ፣ ለተቸገሩት ፈጥነው ሲደርሱ እንመለከታለን። እነዚህ ግለሰቦች ሲያልፉ ደግሞ ተከታዮቻቸው ራዕያቸውን በመጋራት አልያም መልካም ስማቸውን በማስቀጠል በበጎ ምግባር ስራው ላይ ሲሳተፉ አስተውለናል።

ከዚህ በተጨማሪ በልዩ ልዩ ዘርፍ እውቅናን ያተረፉ፣ ለአገር፣ ለማኅበረሰብና ለተወለዱበት አካባቢ ባለውለታ የሆኑ ግለሰቦች መልካም ስማቸው በዘላቂነት እንዲታወስ በሚል ቤተሰቦቻቸው (ስማቸውን ተጠቅመው) ፋውንዴሽኖችን ያቋቁማሉ። በፋውንዴሽኑም ለወጣቶች የትምህርት እድል፣ የሙያ ስልጠና እንዲሁም ሌሎች እውቀቶች ማግኝት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ሲፈጥሩ እንመለከታለን።

ከላይ ያነሳናቸው ጉዳዮችን በምሳሌ ለማስረዳት እንችል ዘንድ የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው ሀገርኛ ዓምዱ ላይ በአንድ ፋውንዴሽን ላይ ትኩረቱን አድርጓል። በዳሰሳውም አገር በቀል ፋውንዴሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ፣ ራዕይውንና ከምስረታው አንስቶ እያከናወነ ስላለው ተግባር በዝርዝር እንቃኛለን። ይህ ተቋም ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ይባላል።

ፋውንዴሽኑ የመካነ-እየሱስ ቤተክርስቲያን ዋና ጸሀፊ ሆነው ባገለገሉት፣ በ1966 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የሉተራን ጉባኤ ካውንስል መስራችና ፕሬዚዳንት እንዲሁም ወንጌልን በማስፋፋት ስራ ላይ ትልቅ ስራ በሰሩት ቄስ ጉዲና ቱምሳ ስም የተሰየመ ነው፡፡

ቄስ ጉዲና ዜጎች መንፈሳዊ ጥንካሬ እንዲላበሱ አጥብቀው ከመስራታቸው ጎን ለጎን የኑሮ ደረጃቸው እንዲሻሻል፣ ከተረጂነት የተላቀቀ አስተሳሰብ እንዲሰርፅ አጥብቀው ይሰሩም እንደነበርም ይገለጻል፡፡

ወጣት ቤተልሔም ንጉሴ ትባላለች። በጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን የማርኬቲንግና ሚዲያ ማኔጅመንት ባለሙያ ነች። እሷ እንደምትለው፤ ፋውንዴሽኑ ከተቋቋመ ከ30 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ለእናቶች እንዲሁም ስራ አጥ ለሆኑ ወጣቶች በተለያየ የሙያ መስክ ስልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቷል። ይህንን ሰልጠና የሚወስዱ የተመረጡ ተሳታፊዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና ስራ የሌላቸው ሲሆኑ፤ በፋውንዴሽኑ እድል ተሰጥቷቸው አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ በማሰብ ስልጠናው ይሰጣቸዋል።

እንደ ወጣት ቤተልሔም ገለፃ፤ ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን በእጅ ሙያ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ስልጠና ይሰጣል፤ በዋናነት በሸክላ፣ በጋርመንት፣ ሸመና እና የቀርከሃ ሰራ ላይ ሰልጣኞች ሙያዊ እውቀትን እንዲማሩ ያደርጋል። ይህን መሰል አካሄድ ለዓመታት ሲከተል መቆየቱን የምትናገረው የሚዲያና ማርኬቲንግ ባለሙያዋ፣ በሚፈለገው ልክ ግን የሰልጣኞችን ኑሮ እንዳላሻሻለ ገልፃለች።

«ሰልጣኞች ሙያዊ እውቀት ማግኘታቸው ብቻ በቂ አልነበረም» የምትለው የሚዲያና ማርኬቲንግ ባለሙያዋ፤ ምክንያቱ ደግሞ ስልጠናውን ጨርሰው ወደ ተሰማሩበት የሙያ መስክ (በሸመና፣ ቀርከሃ ስራ) ላይ የሚያመርቷቸውን ቁሳቁስ ሸጠው ኢኮኖሚያቸውን ለማሻሻልና ስራቸውን ለማስቀጠል የሚያስችል ገበያ አለማግኘታቸው መሆኑን ታስረዳለች።

ፋውንዴሽኑ ሰልጣኞቹ ከነበሩበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እና ስራ አጥነት እንዲላቀቁና ውጤታማ እንዲሆኑ በማሰብ የተቋቋመ ከመሆኑ አኳያ የተፈጠረውን የገበያ ክፍተት ለመሙላት ይፈልጋል የምትለው ባለሙያዋ፤ በዚህ ምክንያት ዳግም ሌላ መላ መዘየድ እንዳለበት በማሰብ ጥናት ማድረግ እና አዲስ ስትራቴጂ መፈለግ መጀመሩን ታስረዳለች። በዚህ ምክንያት ከሙያዊ ስልጠናና የሕይወት ክህሎት ድጋፍ ባሻገር የገበያ ትስስር የሚፈጥር ስትራቴጂ መንደፉንና ተግባራዊ ማድረጉን ትገልፃለች።

«ላሰለጠናቸው ባለሙያዎች የገበያ ትስስር ለመፍጠር በማሰብ ‹ኮኢሊም› የሚባል ሌላ ፕሮጀክት ጀምረናል» የምትለው ወጣት ቤተልሔም ንጉሴ፤ ፋውንዴሽኑ ከሁለት ዓመት በፊት የራሱ ሰልጣኞች የሚያመርቷቸውን እቃዎች በመግዛትና ለገበያ በማውጣት ትስስር መፍጠር መጀመሩን ታስረዳለች። ሰልጣኞቹ በለገጣፎ ልዩ ስሙ ሲሲዲ በሚባል ቦታ ላይ ሙያዊ ትምህርቱን እንደሚወስዱ በመግለፅም በዚያው አካባቢ ከቀርከሀ የተሰራ የሽያጭ ሱቅ በመክፈት ሽያጭ መጀመራቸውንም ትናገራለች።

ወጣት ቤተልሄም እንደምትለው፤ ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን በበርካታ ፕሮጀክቶች ላይ እንደሚሳተፍ የምትናገረው፣ በተለያዩ አካባቢዎች በቡና ምርት፣ በወተት አቅርቦት፣ በተማሪዎች ምገባ፣ በትምህርት እና በሌሎችም መሰል የዜጎችን ኑሮ በሚያሻሽሉ መስኮች ላይ ተሰማርቶ ለዜጎች የእውቀትና ክህሎት ድጋፍ ያደርጋል።

ሰልጣኞቹ የሚመረጡት በጥንቃቄ ሲሆን፣ ፋውንዴሽኑ ከመንግስት ጋር በትብብር ይሰራል። ሰልጣኞቹ የሚመለመሉት መንግስታዊ መዋቅርን በመጠቀም ነው፤ የእጅ ሙያ ስልጠና እንዲወስዱ እድሉ እንደሚመቻችላቸው የምታስረዳው ወጣት ቤተልሔም፤ ይህም ትክክለኛውን ፍላጎት ለመድረስ እንደሚያስችላቸው ትናገራለች። ስልጠናውን የወሰዱ ዜጎች በማኅበረሰቡ ውስጥ እየፈጠሩ ያሉትን በጎ ተፅእኖና ውጤታማነት በአግባቡ ለመለየት ይህንን መሰል ትብብር አስፈላጊ እንደሆነም ትናገራለች።

ለስልጠናው የተመረጡት ነዋሪዎች ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ በቀጥታ ወደ ስራው እንዲገቡ የሚያስችል የፋይናንስ አቅርቦት ፋውንዴሽኑ ከመንግስት ጋር በመተባበር እንደሚያመቻች ትናገራለች። በዚህም 20 በመቶ የሚሆነውን የጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ሲሰጥ ቀሪውን 80 በመቶ ደግሞ ሰልጣኞቹን ከመንግስት አበዳሪ ተቋማት ጋር በማገናኘት ብድር እንዲወስዱ እንደሚደረግ የማርኬቲንግና የሚዲያ ባለሙያዋ ትናገራለች።

ስልጠናውን እንዳጠናቀቁ የፋይናንስ አቅርቦት ወዲያው መመቻቸቱ ባለሙያዎቹ የቀሰሙትን ትምህርት ያለምንም ችግር ወደ ተግባር እንዲያውሉት እድል እንደሚፈጥርም ታስረዳለች። ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ በኮኢሊም ፕሮጀክት በርካታ ዜጎች በፋውንዴሽኑ ስልጠናውን እንዲወስዱ መደረጉን ያስታወሰችው ባለሙያዋ፣ ብደሩን አግኝተው ውጤታማ የሆኑም መኖራቸውን ተናግራለች።

ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን በኮኢሊም ፕሮጀክት ሰልጣኞች የሙያ እውቀት እንዲያገኙ ለማስቻል ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር ይሰራል፤ ከእነዚህ ውስጥ ሚሊንዳ ጌት ፋውንዴሽን አንዱ ነው። ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጭ ለማግኘት ሰልጣኞች የሚያመርቱትን ምርት በመግዛት እና ዳግም ወደ ገበያ በማውጣት የስልጠና ሂደቱ እንዲቀጥልና ሌሎች ዜጎችም የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግም ይሰራል፡፡

«በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች ሕይወታቸውን እንዲያሻሽሉ እድል መስጠት ያስፈልጋል» የምትለው የሚዲያና ማርኬቲንግ ባለሙያዋ፤ ይህንን ለማድረግ የገበያ ትስስር መፍጠሩ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ታስረዳለች። በዚህ ምክንያት በአገር ውስጥ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ የእጅ ሙያ ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ለማድረስ የኮኢሊም ፕሮጀክትን ዓላማ እያስተዋወቁ መሆኑን ታስረዳለች። ይህንን እውን ለማድረግም መንግስት በሚያዘጋጃቸው የገበያ ትስስር መድረኮች ላይ እንደሚሳተፉ ትናገራለች።

በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ በተካሄደው፤ የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት ላይ የሰልጣኞቹን ምርት ለማስተዋወቅ ተሳታፊ እንደሆኑ የምትናገረው ወጣት ቤተልሔም፤ በመድረኩም ማኅበረሰቡን ለመደገፍ እና የበጎ ዓላማው ተሳታፊ ለመሆን እድል የሚከፍት አጋጣሚ ማግኘታቸውን ትናገራለች። ስራዎቻቸውን ባስተዋወቁ ቁጥር ተሳታፊዎች ምርቶችን እንዲገዙ እድል እንደሚያገኙ ገልፃ፤ በምርቱ ተጠቃሚ ከመሆናቸውም ባሻገር ማሕበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ታነሳለች።

ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ ሁሉም አካባቢዎች ላይ ለመድረስ ራእይ እንዳለው ወጣት ቤተልሔም ጠቅሳ፣ በለገጣፎና በየረር አካባቢ (አዲስ አበባ) ያላቸውን አይነት ሱቆች በክልሎች እና ሁሉም ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሹ ታስረዳለች።

የፋውንዴሽኑ ራዕይ በዚህ የተገደበ አለመሆኑንም አንስታም፤ በሙያቸው ብቁ የሆኑ ዜጎች በመፍጠር ለወጪ ንግድ ብቁ የሆኑ አገራዊ ምርቶችን በመላክ በገበያው ላይ ድርሻቸውን ማሳደግ እንደሚፈልጉ ትናገራለች። ይህንን ማድረግ ሲችሉ የሚሰሩ ጠንካራ እጆች እንደሚፈጥሩ ጠቅሳ፣ ፋውንዴሽኑም በመተማመን ከተረጂነትና ከዝቅተኛ ኢኮኖሚ መላቀቅ ዓላማ ማድረጋቸውን ትናገራለች።

ፋውንዴሽኑ በቄስ ጉዲና ቱምሳ ስም የተሰየመበትን ምክንያት ወጣት ቤተልሔም ስታብራራ እኚህ መንፈሳዊ አባት በደርግ መንግስት መገደላቸውን አስታውሳለች። በጊዜው ቄስ ጉዲና ቱምሳ ዜጎች ከመንፈሳዊ ጥንካሬያቸው ባሻገር የኑሮ ደረጃቸው እንዲሻሻል፣ ከተረጂነት የተላቀቀ አስተሳሰብ እንዲሰርፅ ከፍተኛ ፍላጎት እንደነበራቸው ትገልፃለች።

ይህን ራዕያቸውን ለማሳካት በርካታ ጥረቶችን ያደርጉ እንደነበር በመግለፅም፣ ስኬታማ ተግባር አከናውነው ማለፋቸውን ታስረዳለች። የእርሳቸው ሕይወት ሲያልፍም ራዕያቸውን ለማስቀጠል የደርግ ስርዓት ሲያበቃ ልጆቻቸው፣ ዘመድ ቤተሰቦቻቸው እና ጓደኞቻቸው ተሰባስበው «ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን» በሚል መጠሪያ በጎ ምግባራቸውን ማስቀጠላቸውን ገልፃለች።

## እንደ መውጫ

በዓለማችን ታላላቅ የበጎ ምግባር ተቋማት እንዲመሰረቱና ሰብዓዊነት እንዲስፋፋ ግለሰቦች ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ለዚህ ማሳያነት የማሪያ ትሬዛ፣ አበበች ጎበናን፣ የሜቄዶኒያን መስራች ቢኒያምን እና ሌሎች ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎችን ተሻጋሪ ራዕይ መመልከት ይቻላል። በጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽንም ይህንን ራእይ ለመድገም ጥረት እየተደረገ መሆኑን የዝግጅት ክፍላችን እንግዳ ያደረጋት ወጣት ቤተልሔም በዝርዝር አስረድታናለች።

ከግለሰብ ራዕይና ነገን አሻግሮ ከመመልከት ቅን ልብ የሚነሱ መሰል ተግባሮች አገርን ይሰራሉ። በበጎዎች ጥረት፣ በመተባበር፣ በአንድነት፣ አብሮ በመስራትና ማደግን የሚያምን ትውልድን ለመፍጠር ዛሬ አንድ እርምጃን እንደ ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ያሉ አሳውን ሳይሆን አጠማመዱን የሚያሳዩ ፋውንዴሽኖች ያስፈልጉናል። ሰላም!!

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ጉርብትናን ወደ ላቀ የልማት አጋርነት ለመለወጥ

ቴልጌልቴልፈልሶር (የኩሽ አሸክታብ)

የሀገራችን የእቅድ አቅጣጫ ከሆኑ አበይት ጉዳዮች መሀል አንዱ የወደብ ባለቤትነትን ጥያቄ ነው:: ይሄ ሀገራዊ መሻት በተከበረው ምክር ቤት ፊት ለሕዝብ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ንቅናቄዎች ተደርገዋል:: እንደመንግስት ጥያቄው ተገቢ እና አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት በምክንያትና ውጤት በታገዘ ሂደት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሳል ውይይት ተደርጓል::

የወደብ ጉዳይን በተመለከተ እጅግ ዋጋ ያለውና በሁሉም ዘንድ እንደአስታራቂ የሚነሳው ጉዳይ ውይይት የቀደመበት የአብሮ መልማት አቅጣጫ ነው:: እንደመንግስት ያነሳነው ጥያቄ አብሮ የማደግን መርህ የተከተለ እና የእርስ በርስ ትስስርን የሚያጎለብት መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። በስፋት እንደተገለፀው አሁን ባለንበት ወቅታዊ ሁኔታ የወደብ ጥያቄ በብዙ መልኩ አስፈላጊ ነው። ሰፊና የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤትነታችን፣ በየእለቱ የሚጨምር የሕዝብ ቁጥርና አብሮ ከሚመጣው የሕዝብ ፍላጎት፣ እንዲሁም በቀጣናው ካለን ተጽዕኖ ፈጣሪነት አኳያ አስፈላጊነቱ ብዙም፣ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም::

ይህንን ተጨባጭ እውነታ ታሳቢ ባደረገ መንገድም መንግስት ከሱማሌ ላንድ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል:: ኢትዮጵያ ከሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው ስምምነት ማንንም የማይጎዳ በተቃራኒው የንግድና የኢኮኖሚ፣ የደህንነትና የዲፕሎማሲውን ሂደት የሚያቀላጥፍ፤ አብሮ ማደግን መሰረጥ ያደረገ እንደሆነም ይታመናል::

የትብብር ሰነዱ በብዙ ጥናት የተደገፈ በእርስ በርስ ጉርብትናና በአብሮ ማደግ መርህ የተቃኘ መሆኑ የታመነ ቢሆንም በሶማሊያ መንግስት በኩል የግጭት ምንጭ ለማድረግ አላስፈላጊ እሰጣ ገባ ውስጥ ገብቷል:: ኢትዮጵያና ሱማሊያ በብዙ መንገድ የተሳሰሩ፣ የተጎራበቱ ሀገራት ናቸው:: ካላቸው ቅርበትና ጥምረት በሁለቱ ሀገራት መካከል የሚነሱ ማናቸውም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች የሁለቱን ሀገራት ወንድማማችነት ከማጠንከር ባለፈ ለግጭት በር የሚከፍቱ መሆን የለባቸውም::

በተፈጥሮ ጸጋ ተጋግዞና ተመካክሮ አብሮ መልማት፣ አብሮ ማደግ እየተቻለ ለግጭት መንገድ በሚከፍት፤ ለንትርክና ላልተገባ ድርጊት ለሚያጋልጥ ሁኔታ ሀገራቱን ለክተት ተገቢ አይደለም፤ ማንንም ሊጠቅም የሚችል ጉዳይ አይደለም:: የቀደሙ የትብብር እና የጉርብትና ግንኙነቶችን ከማጥቆር ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።

በሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት በጋራ ሀሳብ ለጋራ መድከም፤ጠርነትን በሚሸር የትብብር ማዕቀፍ ውስጥ መሳተፍ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው ወንድማማችነት በሚያስቀጥል፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማህበራዊ ተሳትፎ ባለው የትብብር መንፈስ ውስጥ መቆም ወሳኝ ነው፤ ኢትዮጵያ ያነሳችውም የባሕር በር ጥያቄም ከዚህ አኳያ የተቃኘ ነው::

ኃላፊነት እንደሚሰማው ጎረቤት የኢትዮጵያ መንግስት እና ሕዝብ ለሱማሊያ ብዙ ውለታ ውሏል ነው:: ጎረቤት የሚለው ቃል ተለምዷዊ ስለሆነ ተራ ይመስላል እንጂ እጅግ ዋጋ ያለው ነው። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሉአላዊነት የግዛት መከበር ቅድሚያ ሰጥታ ወታደር በማዋጣት፣ የሰላም ሀሳብ በማቅረብ፣ አስታራቂና አሸማጋይ ሆኖ በመግባት አጋርነቷን ስታሳይ ቆይታለች::

ወዳጅነቷም ለበርካታ ዓመታት በሰላም ማስከበር ስም ወታደሮቿን በመላ የሕይወት መስዋእት ስትከፍል ቆይታላች:: ሀገሪቱ ከአክራሪዎች እና አሸባሪዎች ጥቃት መታደግ የሚያስችሉ ወታደራዊ ስምሪቶችን ወስዳ በጥናት ሰርታለች። ይህ የሶማሊያ ሕዝብ የእለት ተዕለት የምስክርነት ቃል ነው።

በእርግጥ እንደሀገር አይደለም እንደግለሰብ ጉርብትና የላቀ ዋጋ ያለው ነው:: ከጉርብትና ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችም በመከባበርና አብሮነትን ሊያስቀጥል በሚችል መንገድ በትብብር መስራትን ይጠይቃል:: ከባሕር በር ጋር በተያያዘ የተነሳው ጥያቄም ሆነ በሌሎች መሰል ጉዳዮች ላይ የኢትዮጵያ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ በዚህ የትብብር መንፈስ ስር የሚንጸባረቅ ነው::

ኢትዮጵያ በታሪክ አብሮ ከመስራት ባለፈ በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ታሪክ ኖሯት አያውቅም:: የመጣንባቸው ዘመኖች በመካፈልና በማካፈል የሚጠሩ የጉርብትና ዘመኖች ናቸው። ፍትህና ሚዛናዊነት መለያዋ ነው። ቆርሶ ተጋርቶ መብላት እንጂ ራስ ወዳድነትን መገለጫዋ አይደለም።

የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማ የኢትዮጵያንና የሱማሊያን የቆየ ወዳጅነት በማስታወስ ለአብሮ ማደግ ቅድሚያ በመስጠት ሰላም ተኮር መልዕክቶችን ማስተላለፍ ነው:: ኢትዮጵያም ሆነች ሶማሊያ አሁን ባሉበት የኢኮኖሚ እና የሕዝብ ጥያቄ ከሰላም ውጪ ሌላ ነገር የማያስፈልጋቸው ናቸው። ወንድማማችነትን ባስታወሰ በአብሮ ማደግ መርህ መግባባት ቢቻል የወደብ ጥያቄ ይሄን ለግጭት ምክንያት የሚሆን አልነበረም::

ከፍ ብዬ ለማንሳት እንደሞከርኩት የሚሻለው የተሻለውን መምረጥ ነው:: የተሻለው ደግሞ በውይይትና በመከባበር የጋራ ተጠቃሚነትን መፍጠር ነው:: በርሃብና በኋላ ቀርነት ለሚታወቀው ለሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ግጭት ሳይሆን ልማት ነው የሚያስፈልገው:: የግጭት እሳቤዎች በቀደሙት ዘመናት ሀገራቱን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈሉን ቆም ብሎ ማሰብም አስተዋይነት ነው::

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ ከመሆኑ አንጻር፤ በምንም መልኩ ቢቃኝ ተገቢነቱ ያለው የሁሉንም ጎረቤት ሀገራት ይሁንታ የሚጠይቅ ነው:: ከሶማሌ ላንድ ጋር የተደረሰበት የመግባቢያ ስምምነትም በቀጠናው አዲስ የትብብር የታሪክ ምእራፍ የሚከፍት ነው።

ስምምነቱ የሶማሊያን መንግስት ለማስቆጣት ሆነ ወደ አልተገባ መንገድ እንዲሄድ የሚያስገድድ አልነበረም። በተለይም ጥያቄው በአደባባይ ወደብ ላላቸው ጎረቤት ሀገራት የተደረገ ከመሆኑ አኳያ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት የእድሉ ተጠቃሚ መሆን ይቻል ነበር።በሀገራቱ መካከል የነበረውን በመስዋዕትነት የታተመ ወዳጅነት በተሻለ መንገድ ማስቀጠል ይቻል ነበር።

የሶማሊያ መንግስት ስምምነቱን ከመቃወም ጀምሮ ሌሎች /በጉዳዩ የማይመለከታቸው ኃይሎች በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገቡ የሄዱበት የተሳሳተ መንገድ፤ በቀጠናው ዘላቂ ሰላም እንዳይኖር የሚያደርግ፤ የአካባቢውን ሕዝቦች የሰላም እና የልማት ጥያቄ የሚፈታተን ትልቅ ተግዳሮት ነው። በተለይም በሶማሊያ ሕዝብን ቀጣይ ሰላም ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ስለመሆን መገመት አይከብድም።

እንዲህ አይነቱ ያልተገባ አካሄድ፤ ቀጠናው እንዳይረጋጋ ለሚፈልጉ ኃይሎች እንደ ትልቅ መልካም አጋጣሚ የሚታይ ነው። የጥፋት እጆቻቸውን እንዲያስረዝሙ እድል የሚፈጥር ነው። ይህ ደግሞ ለሀገራቱ ሕዝቦች " በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ከመሆን ባለፈ ሊያስገኝላቸው የሚችል ጠቀሜታ አይኖርም። አዋጪው መንገድ የቀደመውን ወንድማማችነትን ማስቀደም፣ የጋራ ተጠቃሚነትን በዋጀ የእርስ በርስ ቁርኝት ጠብ ጫሪ አካሄዶችን መግታት ነው::

የሁለቱ ሕዝቦች የታሪክና የጉርብትና ታሪክ የጠነከረና በቀላሉ የማይላላ እንዳይደለ ብዙ ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል:: እንደባሕር በር ያሉ ሕዝባዊ ጥያቄዎች በብስለት ከታዩ ለመለያየት ሰበብ ከመሆን ይልቅ ለአንድነት ጉልበት የመሆናቸው እውነታ ያመዝናል:: ይህን በሰከነ መንፈስ ማየት ተገቢ ነው።

ከዚህ ውጪ በሶማሊያ በኩል እየታየ ያለው የጠብ ጫሪነት እንቅስቃሴ በድሀ ሀገርና ሕዝብ ላይ ሌላ መከራን ከማወጅ ባለፈ ለማንም ፋይዳ የሌለው መሆኑ ሳይዘገይ ለማወቅ መጣር መልካም ነው:: ሀገሪቱ ከግብጽና ከመሰል ሀገራት ጋር እያደረገችው ያለው ጠብ ጫሪ ወዳጅነት ከጥፋት ውጪ ለሀገራቱ ሕዝቦች የሚያመጣው አንዳች በጎ ነገር አይኖርም::

የአብሮነትን ጎዳና ማቅናት እንጂ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል የጥፋት መንገድ ነገር መጎንጎን ዋጋ የለውም:: ስለፍቅር መቧደን እንጂ ስለጠብ መቧደን ለማንም አይበጅም:: ስለሰላም መመካከር እንጂ ጥፋት መመካከር ትርፉ ኪሳራ ነው:: አዋጪና አትራፊ በሆነ ስምምነት አብሮ መስራት እንጂ የቀጠናውን ሰላም በሚረብሽ ሁኔታ ዘራፍ ማለት የትም አያደርስም::

ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ ለጋራ ተጠቃሚነት በጋራ ሃሳብ የጋራ ብልጽግና ላይ ቢያተኩሩ ነው የሚሻላቸው:: ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብን የወደብ ፍላጎት መረዳት ቀዳሚው ነው:: የሀገሪቱ የወደብ ጥያቄ ከሞራል ሆነ ከዓለም አቀፍ ሕግ አኳያ ተጠያቂ መሆን መገንዘብ፤ ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። በጉዳዩ ዙሪያ የተፈጠሩ አለመግባባቶችን በውይይት ለመፍታት ራስን ማዘጋጀት ተገቢ ነው::

በየትኛውም ጉዳይ ላይ ውይይትን አስቀድሞ አብሮነትን ማስቀጠል ትርፉ በምንም የሚሰላ አይደለም:: ሶማሊያ ልትይዘው የሚገባው አቋምም ይሄ ነው:: የራስን ጥቅም ሳያስነኩ ለወዳጅነት ቅድሚያ መስጠት እጅግ የላቀ የዲፕሎማሲ መርህ ነው:: መከባበርና መቻቻል ካለ ሁሉም ተፈጥሮ በቂያችን ነው::

በየትኛውም ሁኔታ ቢታይ ኢትዮጵያና ሶማሊያ በመከባበር መርህ ተያይዘው ማደግን ካልመረጡ በዛቻና በሰጣ ገባ ማደግ እንዳይችሉ ሆነው የተጎራበቱ ናቸው:: ከኢኮኖሚ ባለፈ የሁለቱ ሀገራት የባህልና የማህበራዊ ትስስር በቀላሉ እንዳይላላ በመሆን አንዳቸው ለአንዳቸው ወሳኝ እንደሆኑ የሚያስረዳ ነው:: ይሄ ወሳኝ ጉርብትና ባልተገባ እሰጣ ገባ እንዳይላላ መከባበርን ባስቀደመ የወንድማማችነት ስሜት ሊታይ ይገባል::


በተለያየ መድረክ ላይ እንደተንጸባረቀው የኢትዮጵያ ፍላጎት አብሮ ማደግ ነው:: ከዚህ ውጪ የሆነ ፍላጎት አልነበረም ወደፊትም አይኖርም። በሕዳሴ ግድብ ላይ የያዝነው አቋም ይሄ ነበር። በባሕር በር ላይም በዚህ አቋም ስር ነን:: የኢትዮጵያ ስልጣኔ አብሮ በማደግ የሚያምን ነው:: ታሪካችን፣ ሀገረ መንግስታችን ሲጸናና ሲመሰረት ጎናችን ያሉን በማጤን ነው:: ስለሆነም ጥያቄአችን ክፋትና ራስወዳድነት የሌለው እንደሆነ ከማንነታችን የሚታወቅ ነው::

ወንድም ከወንድሙ አብሮ ሲሰራ እንጂ ሲቃቃር ደስ አይልም:: ከየትኛው ሀገር በላይ ሶማሊያ ወንድሞቻችን ናቸው:: በነዚህ ሁለት ሕዝቦች መሀል የልማት፣ የእድገት፣ የሰላም፣ አብሮ የማደግ እንጂ የጠብ እቅድ ትርፉማ አይሆንም:: በእውነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራስወዳድነት የማያውቅ ጨዋ ሕዝብ ነው:: ነውር አዋቂ ይሉኝታ የሚገዛው ዘመናዊነትን ከባህልና ከስርዐት ጋር አቻችሎ የሚኖር ነው:: ለአብሮነት ቅድሚያ የሚሰጥ በትብብር የሚያምን መልካም ጎረቤት ነው::

በፍቅር ስም፣ በወንድማማችነት ግብር ከማንም ጋር አብረን ልንሰራ የበረታን ነን:: በጀመርናቸው ለሕዝብ ቅድሚያ በሚሰጡ ጉዳዮች ላይ በጋራ መርህ ለጋራ መስራት ሲወርድ ሲዋረድ ይዘነው የመጣነው መከበሪያ ስማችን ነው:: ለውጥ በውህደት የሚፈጠር የትብብር መንፈስ እንጂ እኔን ብቻ ይድላኝ በሚል አስተሳሰብ የሚወለድ አይደለም። በወንድማማችነት መንፈስ ከሚበልጠው ወደሚበልጠው በመሄድ ድህነታችንን ታሪክ ለማድረግ ለእኛም ለሱማሊያም ያለን እድል ተጋግዞ መስራት ብቻ ነው:: አበቃሁ::

**የኢትዮጵያ ፍላጎት አብሮ ማደግ ነው:: ከዚህ ውጪ የሆነ ፍላጎት አልነበረም ወደፊትም አይኖርም:: በሕዳሴ ግድብ ላይ የያዝነው አቋም ይሄ ነበር:: በባሕር በር ላይም በዚህ አቋም ስር ነን:: የኢትዮጵያ ስልጣኔ አብሮ በማደግ የሚያምን ነው:: ታሪካችን፣ ሀገረ መንግስታችን ሲጸናና ሲመሰረት ጎናችን ያሉን በማጤን ነው:: ስለሆነም ጥያቄአችን ክፋትና ራስወዳድነት የሌለው እንደሆነ ከማንነታችን የሚታወቅ ነው**

# ስፖርት



# ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወጣቶች እጅ ኳስ ዋንጫ አራተኛ ሆና አጠናቀቀች

ዓስማየሁ ግዛው

የአፍሪካ አህጉር ወጣት ወንዶች ከ18 እና ከ20 ዓመት በታች እጅ ኳስ ዋንጫ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ለተከታታይ አምስት ቀናት ተካሂዶ ከትናንት በስቲያ ተጠናቋል፡፡ በውድድሩ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ከ18 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድንም አራተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል፡፡

በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ "ስፖርት ለአህጉራዊ ሰላም" በሚል ሃሳብ የተካሄደው የ2024 የዓለም አቀፍ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ዋንጫ አህጉራዊ ቻምፒዮና ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ከ18 እና 20 ዓመት በታች የወንዶች እጅ ኳስ ብሔራዊ ቡድኖችን አሳትፏል፡፡ ከ10 የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ፣ 11 ብሔራዊ ቡድኖች በሁለቱ የእድሜ እርከኖች ጠንካራ ፉክክር ሲያደርጉ ኢትዮጵያ የደረጃ ተፋላሚ በሆነችበት ጨዋታ ከልምድ ማነስ፣ ቴክኒክ፣ ታክቲክና በአካል ብቃት የበለጠ ውጤት ሳታስመዘግብ አጠናቃለች፡፡

ኢትዮጵያ በውድድሩ ሶስት ጨዋታዎችን ጠንካራ ከሆኑ ሀገራት ጋር አድርጋ አንዱን በመርታት፣ በሁለት ጨዋታዎች ደግሞ ተሸንፋለች፡፡ የመጀመሪያ ጨዋታዋን የዛምቢያ አቻውን 41 ለ 14 በሆነ ውጤት በማሸነፍ በድል መጀመር ችላ ነበር። በሁለተኛው ጨዋታ ጠንካራዋንና ቻምፒዮን የሆነችውን ናይጄሪያን ገጥማ 47 ለ31 በሆነ ውጤት ተሸንፋለች፡፡ በዚህም በደረጃ ጨዋታ የካሜሩን ብሔራዊ ቡድንን ገጥማ 45 ለ 37 በሆነ ውጤት ተረታ ሜዳሊያ ውስጥ ሳትገባ ውድድሩን ፈጽማለች፡፡

የኢትዮጵያ ቡድን በልምድ ማነስ፣ ቴክኒክና ታክቲክ እንዲሁም በአካል ብቃት በተጋጣሚዎቹ ቢበልጥም ትልቅ ልምድ ቀስሞ ውድድሩን ማጠናቀቁን የቡድኑ ዋና አሰልጣኝና ተጫዋቾች ተናግረዋል፡፡ የብሔራዊ ቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ኢንስፔክተር ተስፋዬ ሙለታ፣ በውድድሩ ከሁሉም ዞኖች የተውጣጡ ጠንካራ ቡድኖች ጋር በመጫወታቸው የጠበቁትን ውጤት እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡ ቡድኑ ከረጅም እረፍት በኋላ ወደ ውድድር እንደተመለሰ የጠቀሱት አሰልጣኙ፣ ይህም በብዙ ነገሮች እንዲበለጥ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ቡድኑን ተሰባስቦ በአካል ብቃት፣ ቴክኒክና ታክቲክ ላይ ዝግጅት ለማድረግ የነበረው ጊዜ አጭር ቢሆንም፣ ጥሩ ዝግጅት በማድረግ ወደ ፉክክር መግባቱንም አስታውሰዋል፡፡



ፎቶ፡- ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

ኢትዮጵያ አህጉራዊ ውድድሩን በስኬት ማስተናገድ ችላለች፣

ናይጄሪያና ካሜሩን በእጅ ኳስ ስፖርት ትልቅ ደረጃ ላይ የሚገኙ እንደሆኑ የሚጠቅሱት አሰልጣኙ፣ በአካል ብቃት፣ በቴክኒክና ታክቲክ፣ ከፍተኛ ብቃት ላይ መድረሳቸውን ገልጸዋል፡፡ የማገገሚያ ጊዜ አለመኖርና በየቀኑ የመጫወት ልምድ ማጣት የኢትዮጵያ ቡድን ላይ ጫና ፈጥሯልም ብለዋል፡፡ በውድድሩ የተሻለ ውጤት ባይመዘገብም የስልጠና እና ምልመላ መንገዱ መፈተሽ እንደሚኖርበት ትልቅ ልምድ ማግኘታቸውንም ገልጸዋል፡፡ በስፖርቱ የእድሜ ጉዳይ አሁንም ትልቅ ጥያቄ የሚያጭርና ትኩረት ተሰጥቶት መስራት የሚገባው ጉዳይ ሲሆን፣ ለዚህም የእጅ ኳስ ማሰልጠኛ አካዳሚ አለመኖር ትልቅ ችግር እንደሆነም አክለዋል፡፡ በፕሮጀክቶች ላይ የሚሰራውም ስራ ተመጋጋቢና ታዳጊዎችን ማፍራት የሚያስችል መንገድን መከተል እንደሚኖርበት አመላክተዋል፡፡ የትምህርት ቤቶች እጅ ኳስ ውድድር ትኩረት ተሰጥቶበት መካሄድ እንደሚኖርበትም አስቀምጠዋል፡፡

ከወጣት ብሔራዊ ቡድኑ ተጫዋቾች አንዱ የሆነው ስጦታው ፍቃዱ በበኩሉ፣ ኢትዮጵያ ውድድሩን በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ ትልቅ ዝግጅት ማድረጓንና ለዚህም ወጣት ብሔራዊ ቡድኑ የምሥራቅ አፍሪካ ዋንጫን ማንሳቱ ምክንያት እንደሆነ አስታውሶ፣ ቡድኑ የተሻለ ዝግጅት በማድረግ ውድድሩን በድል እንደጀመረ ተናግሯል፡፡ በእጅ ኳስ ችሎታ የተሻለ ደረጃና ብቃት ላይ የሚገኙ ሀገራትን በመግጠማቸው አራተኛ ደረጃን ይዘው ማጠናቀቃቸውንም ገልጿል፡፡ ኢትዮጵያ በአህጉር አቀፍ ውድድር በመሳተፏ የተሻለ ልምዶችን መቅሰማቸውን አስረድቷል፡፡ ውድድሩ ኢትዮጵያ በመካሄዱ የእጅ ኳስ ስፖርትን በከፍተኛ ደረጃ ማነቃቃት መቻሉንና ውድድሮች ቤት ውስጥ እንዲካሄዱ፣ የዳኝነትና የስልጠና መንገዶች መፈተሽ እንደሚኖርባቸውም አስተያየቱን ሰጥተል፡፡

ከ18 ዓመት በታች በተካሄደው ከፍተኛ የዋንጫ ፉክክር ናይጄሪያ ጊኒን 38 ለ 26 በመርታት የዋንጫና የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆና አጠናቃለች፡፡ ጊኒ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ የብር ሜዳሊያ ይዛ ስታጠናቅቅ፣ ካሜሩን ኢትዮጵያን በደረጃ ጨዋታ አሸንፋ ሶስተኛና የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት ሆናለች፡፡ ከ20 ዓመት በተካሄደው ውድድር ርዋንዳ ኮንጎን በመርታት ዋንጫ አንስታለች። ኮንጎ ሁለተኛ ደረጃን ይዛ ስታጠናቀቅ ሪዩኒየን ሶስተኛ ደረጃ ይዛ ውድድሩን ፈጽማለች፡፡

የናይጄሪያ ከ18 ዓመት በታችና የርዋንዳ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኖች አፍሪካን በዓለም እጅ ኳስ ዋንጫ አፍሪካን ወክለው የሚሳተፉ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ታዳጊና ወጣት ብሔራዊ ቡድኖች የተሳተፉበት፣ ይህ ውድድር 6 ከ 18 ዓመት በታች 5 ከ20 ዓመት በታች በአጠቃላይ 11 ብሔራዊ ቡድኖች ተወዳዳሪ ሆነዋል። ኢትዮጵያ፣ ማዳጋስካር፣ ጊኒ፣ ካሜሩን፣ ዛምቢያ እና ናይጄሪያ ከ18 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኖቻቸው ሲወዳደሩ፤ ሪዩኒየን፣ ዚምባቡዌ፣ ርዋንዳ፣ ጊኒ እና ኮንጎ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኖቻቸውን አወዳድረዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር CC/SBO/02/2017/2024

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጉምሩክ ኮሚሽን የሰመራ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ የሚያስፈልጉ የተለያዩ እቃዎችን በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

1. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጉምሩክ ኮሚሽን የሰመራ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት የተለያዩ በስድስት ሎት የተከፋፈሉ እቃዎችን ሎት1፡- የፅህፈት መሳሪያዎች/6212/ የፅዳት መሳሪያዎች/6218 እና የህትመት እቃዎች/6213/ ሎት 2፡- ከአንድ ዓመት በታች የሚያገለግሉ እቃዎች/6219/ ሎት 3፡- የግንባታ እቃዎች/6244/ ሎት4፡- የቢሮ ቋሚ እቃዎች/6313/ እና የቢሮ ቋሚ እቃዎች/6314 ሎት 5፡- የተሽከርካሪ እቃ መሳሪያዎች /6241/ ሎት 6፡- የደንብ ልብስ /6211/ ብቃትና ፍላጎት ያላቸውን ተጫራቾች በብሄራዊ ግልጽ ጨረታ መወዳደር ይችላሉ፡፡
2. ጨረታው የሚከናወነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት በመንግሥት ግዥ አዋጅ በተገለጸው ብሄራዊ ግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡ በሎት የተከፋፈሉ እቃዎችን ግዥ ጨረታ የሚከናወነው ብቁ ከሆነ ተጫራች እና ከአቅርቦቱ ጋር አግባብነት ያላቸው ሆኖ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ስራ ፍቃድ ያለው፣ የዘመኑን ግብር መክፈላቸውን የሚገልጽ ታክስ ክሊራንስ፣ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ (በአዲሱ ስሙ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን) ዌብሳይት ላይ የአቅራቢነት ዝርዝር (Supplier List) ፕሪንት አርጎ ማምጣት አለባቸው፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፍኬት ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች በዚህ ጨረታ ለመሳተፍ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ከፍለው የጨረታ ሰነዱን ከዚህ በታች በተገለጸው አድራሻ በአካል በመገኘት መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. የጨረታው አሸናፊ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና 10% (አስር በመቶ) C.P.O በማስያዝ ከመስሪያ ቤቱ ጋር ውል ይፈራረማል፡፡
5. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 7(ሰባት) በተገለጸው አድራሻ ጨረታው ከወጣበት ጥቅምት 29 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሕዳር 13 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ 4፡00 ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡፡ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሕዳር 13 ቀን 2017 ዓ.ም ጠዋት 4፡30 ሰዓት ላይ ይከፈታል፡፡ ዘግይተው የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም፡፡
6. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ለእያንዳንዱ ሎት ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) በሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. የጨረታው ሰነድ የሚገባበት አድራሻ ጉምሩክ ኮሚሽን ግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት 4ኛ ፎቅ ግዥ ቡድን ቢሮ፡፡
8. ቅ/ጽ/ቤቱ በከፊልም ሆነ በሙሉ ጨረታውን የመሰረዝ መብት አለው፡፡

የጨረታ ሰነድ መሸጫና ጨረታ መክፈቻ ቦታ ጥላሁን ገሰሰ አደባባይ መሿለኪያ አካባቢ የሚገኘው የኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት (ይርጋ ኃይሌ ፕላዛ ህንጻ) ግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ቡድን 4ኛ ፎቅ

**ስልክ ቁጥር:- 0333668839/0926632123/0945091748/0917351151/**

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጉምሩክ ኮሚሽን የሰመራ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**



## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የቁም ደን ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር OFWE/GU-04/2017

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ወለጋ ቅ/ጽ/ቤት ቄ/ወለጋ እና ምስራቅ/ወለጋ ዲስትሪክቶች ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ፤ የ"Pinas Patula" እና የፈረንጅ ጥድ ድብልቅ ግንዲላ፣ አርሲ ቅ/ጽ/ቤት አዳባ ዶዶላ ዲስትሪክት ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ ግንዲላ፤ ኢሉ አባ ቦራ ቅ/ጽ/ቤት ሲቦ ቶሊ ቆቦ እና ያዮ ዲስትሪክቶች ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ፤ የ"Grevillea robusta" እንዲሁም የ"Pinas Patula" እና "Grevillea robusta ድብልቅ ግንዲላ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

**ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ**

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ሀረርጌ ቅ/ጽ/ቤት ጀሎ ሙክታር ሃደስ ዲስትሪክት ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ ግንዲላ እና ኢሉ አባ ቦራ ቅ/ጽ/ቤት ገባ-ድዴሳ ዲስትሪክት ላይ የ"Grevillea robusta" ግንዲላ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም:-**

1. የግንዲላ እና የእንጨት መሰንጠቂያ የታደሰ ንግድ ፈቃድ የቫት (VAT) ተመዝጋቢና "TIN number" ያላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች እንዲሁም ስለጨረታው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ የጨረታ ሰነድ ለእያንዳንዳቸው የማይመለስ 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ቀበና ሼል/ አይል ሊቢያ አጠገብ በሚገኘው የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 201 እና ጨረታው በወጣበት አርሲ ቅ/ጽ/ቤት ነጌሌ አርሲ ከተማ፤ ሀረርጌ ቅ/ጽ/ቤት ጭሮ ከተማ፤ ኢሉ አባ ቦራ ቅ/ጽ/ቤት መቱ ከተማ እና ወለጋ ቅ/ጽ/ቤት ጊምቢ ከተማ በመግዛት በጨረታው መሣተፍ ይችላሉ፡፡
2. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው ለ15 ተከታታይ ቀናት ሲቆይ ለሁለተኛ ጊዜ የወጣው ደግሞ ለ10 ተከታታይ ቀናት ይቆያል።
3. ጨረታው የሚዘጋበት እና የሚከፈትበት ትክክለኛው ቀንና ሰዓት በጨረታው ሰነድ ውስጥ ይገለጻል፡፡
4. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid bond) የሚሆን ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ 5% በማስላት በድርጅቱ ዋና መ/ቤት የምትጫረቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ባንኮች በቅ/ጽ/ቤት የምትጫረቱ መ/ቤቱ ከሚገኝበት ከተማ በባንክ በተረጋገጠ ደረሰኝ (CPO) ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል።
5. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር:- 0111240249**

**በመደወል መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

**የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት**